# የገብረክርስቶስ ደስታ ግጥሞች



በአሉ ግርማና ባለቤቱ ከገብረክርስቶስ ደስታ ጋር (1963 አም)
ከአቶ ሳሙኤል አለማየሁ ታዬ የፎቶግራፍ ስብስብ የተገኘ

# ማስታወሻ

*ሰላም ኣምሃ*

*ቁም ነገረኛው ወዳጄ፥ ኣቶ ኣማረ ማሞ (ደራሲ፥ ኤዲተርና ኣሳታሚ) ከየጋዜጣውና ከየሰዉ ኣሰባስቦና ጠርዞ ከኣዲስ ኣበባ የላከልኝን የዝነኛውን ሰኣሊና ገጣሚ የገብረክርስቶስ ደስታን ግጥሞች እን ድትመለከታቸው ልኬልሃለሁ። ገብረክርስቶስ ደስታ፥ ኣፈር ይቅለለውና፥ በቅርብ የማውቀው ታላቅ ኢትዮጵያዊና የስነጥበብ ሰው ነበር። ግጥሞቹ በመፅሃፍ መልክ ታትመው ስላልወጡና ስላልተሰራጩ ብዙ ሰው በተለይም ወጣቱ ትውልድ ኣያውቃቸውም፥ የስእሉን ያህል። ስለዚህ የሚያመችህ ከሆነ ኣልፎ ኣልፎ ኣንዳንዱን ግጥም በEEDN ላይ ብታወጣው ጥሩ ነበር። ኣምሃ፥ በነገራችን ላይ ከኣስራ ኣምስት ኣመታት በፊት በጣም የማከብረውና የማደንቀው ወዳጄ፥ ሙዋቹ ኣቶ ሰዩም ወልዴ ራምሴ የገብረክርስቶስን ግጥሞች ከየቦታው ሰብስቦና መግቢያ ፅፎለት ኣስተይቦት እንደነበር ኣስታውሳለሁ።*

*ኣሰፋ ገብረማርያም ተሰማ*
*ላስ ቬጋስ፥ ኔቫዳ*
*Oct. 8, 2005*

እንግዴህ፥ ከላይ እንዳነበባችሁት ግጥሞቹን የሰበሰቡት ኣቶ ኣማረ ማሞ ሲሆኑ፥ ለኔ የደረሰኝ በኣቶ ኣሰፋ ገብረማርያም ተሰማ በኩል ነው። በተጨማሪም፥ እነዚህን ግጥሞች ስተይብ ያደረግሁዋቸውን የፊደልም ሆነ የሃሳብ ስህተቶች፥ ኣቶ ቴዎድሮስ አበበ፥ ኣቶ ኣሰፋ ገብረማርያም ተሰማ እና ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ሙከራየን ኣንብበው ኣርመውልኛል።

ፅሁፎቹ ብዙ የማይታዩና የደበዘዙ ቃሎች እንዲሁም የፊደል ስህተት ኣለባቸው። ለማስተያየትና ለማረም እንዲመች፥ የኣቶ ገብረክርስቶስ ግጥሞች ወይም ስለ ኣቶ ገብረክርስቶስ የተፃፉ ሰነዶች ያሉዋችሁ ሁሉ

በ Asfawa@Missouri.edu

*ወይም*

Amha Asfaw
P.O. Box 7134
Columbia, Mo 65205-7134

ብትልኩልኝ ኣመሰግናለሁ።

የሚከተሉትን፥ የኣቶ ገብረክርስቶስ ደስታን ግጥሞች እንደምትወዱዋቸው ተስፋ ኣደርጋለሁ። «ሃገሬ»ን ስታነቡ፥ ሞቱ እንደተመኘው በሃገሩ ሳይሆን በሰው ሃገር መሆኑን ኣስታውሱ። ያሳዝናል።

የማይነበቡ ቃሎችን ምን እንደነበሩ መገመት ከቻልኩ፥ በፋንታቸው የመሰሉኝን ቃሎች ኣስገብቻለሁ፤ ትክክል የማይመስሉ ቃሎችን ሳገኝ ለውጫቼዋለሁ፤ ኣንዳንድ ለማንበብ ያስቸገሩኝን ስንኞች ደግሞ ኣቀማመጣቸውን ቀይሬኣለሁ። ሆኖም፥ ያደረግሁዋቸውን ለውጦች በግርጌ ማስታወሻ ውስጥ ለማሳየት

ሞክሬኣለሁና ኣቶ ኣማረ ማሞ የሰበሰቡኣቸው ግጥሞች ምን ይመስሉ እንደነበረ ማወቅ ኣያስቸግርም። ሌላው ለውጥ የፊደል ስርኣት ስለሆነ ግጥሙን የሚያዳምጥ ሰው ሊገነዘበው የሚችል ልዩነት ኣይኖርም። ሶስተኛው ለውጥ የስንኞቹ ኣደራደር ነው። ይህም እንደኣንባቢው የማዜም ስልት የሚቀያየር ነውና የግጥሞቹን መሰረት ኣያናጋውም። ከባዱ፥ የማይነበቡትን ወይም ተነበው ትርጉም የማይሰጡትን ቃሎች መለወጡ ነው። ይህ ደግሞ ኣቶ ገብረክርስቶስ ደስታ በእጃቸው የጻፉት ወይም ያረሙት ቁልጭ ብሎ የሚነበብ ቅጅ ካልተገኘ ወይም ደግሞ ብዙ የተለያዩ ቅጅዎች ተገኝተው ኣንዱን ካንዱ እያመሳከሩ የተሻለውን መምረጥ ካልተቻለ የማይቀር እዳ ነው።

«አ» ግእዙና «ኣ» ራብኡ እንዲሁም «ሀ» ግእዙና «ሃ» ራብኡ ድምጻቸው ኣንድ ስለሆነና የኢትዮጵያ ቁዋንቁዋዎች (ኣካዳሚው እንኩዋ «ቋንቋዎች» ነው የሚለው) ኣካዳሚ የግእዙን ቦታ ለ«ኸ» እና ለ«ኧ» ትቶ (ሲለመድ ማለት ነው) ራብኡን ብቻ ስለሚጠቀም፥ ተከትየዋለሁ። ሆኖም፥ የቁዋንቁዋ ኣካዳሚውን ውሳኔ በሙሉ ኣልወሰድኩም፤ የምወደውን ብቻ ነውና እየመረጥኩ የማከብረው። ለምሳሌ «የመጀመሪያ ቀን» የተባለውን ግጥም ሁለት ቦታ ተጽፎ ኣግኝቼዋለሁ። ያልታተመው (በጽህፈት መኪና የተተየበ ስለሆነ) ኗ፥ ጇ ሲል፥ የታተመው ግን ንዋ፥ ጅዋ ይላል። እኔ ግን፥ እንደ ጇ ያሉትን ፊደሎች ሁሉ ጅዋ፥ ጁዋ ወይም ጁኣ እያልኩ ለውጫቼዋለሁ።

ኣብዛኞቹ ግጥሞች የተፃፉበትንም ቀን ሆነ ቦታ ኣያመለክቱም። የተፃፉትም ቀኖች የተከተሉት ኣቆጣጠር ኣመተ ምህረት ይሁን ኣመተ እግዚእ ኣያሳዩም። ግን ኣመተ ምህረት ሳይሆኑ ኣይቀሩም። ኣንዳንድ ግጥሞች «የዛ.ኢ.» የሚል ምህፃረ ቃል ከግርጌያቸው ተፅፎባቸው እናገኛለን። የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ ላይ የታተመ ወይም በዚያ ጋዜጣ ላይ ከታተመው የተቀዳ ማለት ይመስለኛል።

ኣምሃ ኣስፋው።
ታህሳስ ፱ ቀን ፲፱፻፺፰ ኣ.ም

# ምንድን ነሽ

ነፋስ ወይም ኣየር ውሃ ነሽ እንፋሎት
መልኣክ ወይም ሰይጣን ብርሃን ወይም ፅልመት
ኣልተረዳሁትም ስራሽን በቅጥ
ድንጋይ፥ ኣፈር፥ ጭቃ፥ ቅጠል፥ እንጨት፥ ሊጥ
ብረት፥ ነሃስ፥ መዳብ፥ ወርቅ፥ ሉል፥ ኣልማዝ
ኣገልጋይ ለስራ፥ ለጌጥ የሚያዝ
ቀይ ነሽ፥ ቢጫ ነሽ፥ ኣረንጉዋዴ ጥቁር
ሃምራዊ ቡና ኣይነት፥ ቀለምሽ የሚያምር።
ፋንጋ ነሽ ሰልካካ ቆንጆ ወይም መጥፎ
የማር እንጀራ ነሽ የወጣ ከቀፎ
ወለላው በጌሾ በውሃ ተጣርቶ
ናላየን ያዞረው ከቦታው ኣናግቶ
ኣጭር ነሽ ረጅም ወፍራም ወይም ቀጭን፥
ወርድና ስፋትሽ ልኩ ምን ይሆን።
እያለሽ የለሽም ሳትኖሪም ኣለሽ
ጣፍጠሽ የምትቀሪ ማር ወለላ[1] ነሽ።
የምታቃጥይ ቃሪያ ነሽ በርበሬ
እሳት ለብላቢ ነሽ ኣከሰልሽኝ ዛሬ።
ነገ ስትሄጅ የለሁም ትቢያ ነኝ[2]
እርግጥ የፈጣሪ ነሽ ወይ እስትንፋስ
እውነት ቀሪ ረቂቅ የማይዳሰስ
ሃይሌ ነሽ ምርኩዜ ብርታቴ ጤናዬ
ጠጉሬ ግንባሬ፥ ኣይንና ኣፍንጫዬ
ኣፌ ጆሮዬ ነሽ ጥርስና እስትንፋሴ
ኣንጎሌ ነሽ ኣንቺ የግሬ የጄ ጌታ
ደግፈሽ የያዝሺኝ የሆንሺኝ መከታ
ኣልጋሽ ነኝ ፍራሺሽ መከዳ ልብስሽ
የምትዳብሽን ስትንቀሳቀሺ
ጥላሽ ነኝ እርምጃሽ ግዞተኛ ላንቺ
ስለቀቅ የምሮጥ ኣስረሽኝ ስትፈቺ
መኖርሽን እንጃ ስሜትሽ ህልም ነው
የራቀው ሰማይ ነሽ የማይዳሰሰው
የተረሳሽው ነሽ ያለፈው ትናንት፥
ማነው የሚያስብሽ እሌለሁበት።
ሽቱና ቅባትሽ የታለው መኣዛ፥
የውሃ ሽታ ነው የተነሳው ለዛ።
ጌጥ ወዴት ይሆን የለም ቅስቃሴ[3]
ገዳም የገባ ነው የሞተ መነኩሴ።
የምትጫወችው ሙዚቃ የታለ?
ኣፌና ምላሴ ድምፄም ዝም ካለ።
እኔ ነኝ የሆንኩት ሳላውቀው ኣንቺን፥
ለኔ ብዬ ላንቺ ጤና ስለምን።
ባሳብ መሳሪያ የፈጠርኩሽ እኔ፥
ቦታም የሰጠሁሽ ፅድቅና ኩነኔ፥
በቅርፅ ኣሳምሬ በቀለም ቀብቼ፥
የእግዚኣብሄርን ፀዳል ብርሃኑን ሰጥቼ።
የኔን ማየት መስማት መሆኑን ሳላቀው
ሳላቀው መሆኑን ሃሳቤን ቢሞላው።

---

[1]ኣይነበብም፤ ኣራሚዎች ግን «ወተቴ» ለማለት የሞከሩ ይመስላል።
[2]ከዚህ ስንኝ ጋር የሚገጥም ሌላ ስንኝ የለም፤ ሳይፃፍ ተረስቶ ይሆናል።
[3]የጎደለ ነገር ያለ ይመስላል፥ ትርጉም የለውም።

የሳንባዬ ወናፍ የልቤ ጭፈራ፥
የደሜ መርዋርዋጥ የጉልበቴ ስራ
ኣንጎሌ መንፈሴን እያውለበለበው፥
ትንፋሼ እሳቱን እያቀጣጠለው፥
ገላዬ ሲጣጤስ ሲቃጠል ሲፍም፥
ስበላ ሲሞቀኝ ስሮጥ ስደክም፥
የፍጥረት ግዴታ ኣካሌን ሲሰራው፥
እየቆሰቆሰ ህይወት ሚመግበው፥
ኣለሁ ብዬ ሳስብ ኣንቺ ነሽ ምክንያት
ማነሽ በኑሮዬ ቤት የሰራሽበት።
ምንድንነሽ? ምንድንነሽ? ምንድንነሽ? ምንድንነሽ?
ካንቺ ጋር እያለሁ ሳውቀው የማላውቅሽ፤
ቅመም ነሽ ዝንጅብል ቅርንፉድ ቀረፋ፥
የነጠረ ኣረቄ የእህል ኣረፋ።
የሚያንገዳግደኝ እግሬን ያሳሰረው፥
ምንድነው ጥንስሱ ለይቼ ልወቀው፤
ወዴት ነው ቀበሌሽ መደበቂያሽ ዋሻው።
ወይም ባዶ ቦታ ኣይን የማይደርስበት፥
ጫጫታ ሁካታ ጩኸት የሌለበት፥
እንቆቅልሽ ነፍሴ ንገሪኝ በርጋታ፥
ጨንቆኛል ጠቦኛል ያለሽበት ቦታ።
ነፍሴ ተገለጭ መኖሬን ላስታውስ፥
　　　የት እንደምትቀሪ፥
　　　ምን እንደምትፈቅጂ፥
　　　ምን እንደምትሰሪ፥
　　　ስወለድ ጀምሮ ኣብሮኝ የሚኖረው፥
　　　የሚንቀሳቀሰው፥
ይኸ ሰውነቴ ሲበተን ሲፈርስ።

◆ 25/1/49

# ይኸ ጊዜ

ሃቻምና በረረ
ኣምናም ተሻገረ
ዘንድሮም ይሮጣል
ህፃን እያደገ ልጅ ይጎለምሳል።
ይጠፋል ኣሮጌው ወጣት እያረጀ
ጊዜ እየደረጀ።
ተከማችቶ ኣይሞላም
እንደምን በረረ፥ ይገርማል፥ ኣይቆምም።
መስከረም ሲቀባ ቀለም ባመት ባመት
ኣልተወም ማደሱን ያረጀውን ፍጥረት
ያዳፈነው መሬት።
ክረምትም ሲገባ ማጠቡን በውሃ
በተራው ሲተካ በጋም ከበረሃ
ኣልተወም ይሰፋል
ሁሉም ይንፍዋቀቃል
ገመዱን ሲጎትት ጊዜ ይቀልዳል።
ምን ይሆን ይህ ጊዜ?
የሰኣት እጆቹ ድምፁ ውዝዋዜ።

ወይም የሰው እድሜ ሰባና ሰማኒያ
ያመት መለወጫ የዘመኑ ጣቢያ።
ወይ ቀንና ሌሊት
ወይ መወለድ መሞት፥
ወይም ያለም መዞር የፀሃይ መታየት
ሙሉዋ ጨረቃ፥ የጨረቃ መጥፋት።
ጊዜ ይኸ ይሆን?
ሰው ነው የሚሄደው ጊዜን እየለካ?
ወይስ ጊዜ ቆምዋል ምንም ሳይነካ?
ምናልባትም ደግሞ ኣብረው ይሄዳሉ
እየተቻኮሉ፥
ወደሁዋላው ሲቀር ፍጥረት በድካሙ
ጊዜ ይራመዳል ሲቃለል ሸክሙ።
ባንድ በኩል ደግሞ ጊዜ ፍፁም የለም
መነሻ መድረሻ መካከል የለውም።
ሰው ነው የሚለካው
ፀጥታን ሰንጥቆ ድምፅ እንደሚወጣው።
ጨለማን ሲረታ
ብርሃን እንደሚገኝ በጠቆረው ቦታ።
ሰውም በጊዜ ላይ
ይሆናል መስታወት መኖሩን የሚያሳይ።
እንዳይሆን ያስፈራል
ይኸም እንዳይባል፥
ሰው ቢኖር ባይኖርም መሬት መሽከርከርዋን
ወር እየቆጠረች ጨረቃም መውጣትዋን
ባህር መላወሱን፥ ዝናብ ማርከፍከፉን
ኣፈር መንፍዋቀቁን፥
ኣይተውም ስራውን ምንም ኣያቋዋርጥ
ሰው ነው ተመልካቹ በዘመን ላይ ሲሮጥ።
ውሸት ነው ይጠፋል
ጊዜም እንደሌላው
ጊዜም ከሚወደው
ጊዜም ከጊዜው ጋር ሞቶ ይቀበራል።
የነቢያት ጊዜ ዛሬ ወዴት ኣለ?
የነቄሳር ጊዜ ዛሬ ወዴት ኣለ?
ጂንጂስካን ግዛቱ
የሂትለር ኩራቱ።
ዛሬ ወዴት ኣለ?[1]
ዛሬ ወዴት ኣለ?[1]

◆ 18/4/50

# የሚያፅናኑ

ጌጣማ[2] ብረት
          የግድግዳ
ጅምር ስራ
     በየጊዜው የሚያድግ
               ቀን የሚገፋ

---

[1]በእጅ የተፃፉ ናቸው። ሌላ ሰው ያስገባቸው ይመስላል።
[2]«ጣ» በደንብ ኣይነበብም። ግን «ጌጣማ» ይመስለኛል።

ትንሽ ክፍል
ከአለም ጣጣ የምትከልል
ትንሽ ወንበር
የምታቅፍ
የምትደግፍ
አሮጌ ልብስ
አብሮ ያረጀ
የነተበ
አሮጌ ጫማ
ያገለገለ
የሰፋ
ማንቆርቆሪያ ሳህን
ውሃ
ውሃ መታጠቢያ
ፎጣ የሚሻክር[1]
ምድጃ ከሰል እሳት
እሳት ሙቀት
ቁራሽ ዳቦ
ወተት በጠርሙስ
ፍሬ በሳህን
ሲጃራ
የተጋመሰ
የሚጤስ
የጎረቤት ሙዚቃ
ከሩቅ የሚመጣ
ደብዳቤ
ማስታወሻ ደብተር
ጋዜጣ
የዘመድ
ፎቶግራፍ
የወዳጅ
የራስጌ መብራት
የግድግዳ ጥላ
የተሰቀለ ስእል
መፃህፍት
መፃህፍት
መፃህፍት
መጠጊያ
መሸሺያ
መደበቂያ
የሚያጫውቱ
የሚያስተምሩ
የሚያነጋግሩ
አልጋ ፍራሽ ትራስ
የሚውጥ አልጋ
የሚያሳርፍ
እንቅልፍ
እንቅልፍ
እንቅልፍ

---

[1]«የሚያሻክር» ነበር የተፃፈው። የሚሻክር ሳይሆን አይቀርም።

እንዲሁም ሌላ
        እንዲሁም ብዙ
                        ብዙም ሌላ
ያፅናናሉ።

◆ ሃምሌ 18/1950 በስነጥበብ ት.ቤት/የዛ.ኢ. ነሃሴ 30/1950

# ባለ ክራር

ኣሰማ ዜማህን
በክራሩ ጅማት የሚነደፈውን።
ጣቶችህ ይዝለሉ እያሸበሸቡ
ኣድማጭ ይሰብስቡ።
ሙዚቃን ኣንስተህ ጣለው በሙዚቃ
የፈዘዘው ይንቃ፤
የተኛው ይቀስቀስ
ይሽከርከር ይደንስ።
ዝፈን እባክህን
ኣንቺ ልጅ ገላግሌን፤
እንካ ባለክራር
ተቀበለኝ ግጥም ዝፈን ስለፍቅር፤
«ኣንቺ ሳሚኝና እኔ ልመጥምጥሽ
የሰው ስጋ እርም ነው ጨርሼ እንዳልውጥሽ።»
እንካ ስለኑሮ ተክዝ ግጥም ይዘህ
ወዳጅ ማለት ብለህ።
ወዳጅ ማለት በሞት በህይወት በኑሮ
ነፍስና ስጋ ነው የሚጨነቅ ኣብሮ።
ለውጠው ዜማህን ኣጉረምርም ኣቅራራ
የሚሮጠው ይቁም የሄደው ይጠራ።
ጥቂት ሞቅ ይበልህ
የፈራ ይርበድበድ
ይራድ . . . ሰውነቱ ይራድ . .[1]
ባለወኔው ጀግና ይሰብሰብ ከደጅህ
ደሙንና ቁስሉን ጠባሳውን ይዘህ[1]
ኣምጣው ጦርነቱን በዜማ ለውጠህ።
የፍቅር ጋብቻ ድግሱ ተሰርቶ
ባይናችን ላይ ይምጣ ቀርቦ ተሰናድቶ።
ኣምጣው የጠፋውን ኣምጣው ያለቀውን
ኣምጣው የሄደውን፤
መልሰው ጊዜውን ይታይ መስታወቱ
ጣትህ ይወልውለው ያሳየኝ ጅማቱ፤
ላላፊ ላግዳሚው ከመንገድ ላይ ሆነህ
ይሰማ ቅኝትህ፤
የሚስረቀረቀው[2] ድምፅህ ብዙ ይሂድ
እያጀበ ዘመድ።
ሙዚቃን ኣስተምር ትርጉሙን ኣስረዳ
የሰው ስሜት ዝረፍ ሃሳብን ኣስከዳ።
ሂድ ወደበረሃ ግባ ወደ ጫካ

---

[1]በእጅ ፅህፈት የተጨመሩ ስንኞች ናቸው። ኣቶ ገብክርስቶስ ሳይሆኑ ሌሎች የጨመሩዋቸው ይመስላሉ። «ሰውነቱ» የሚለውን ቃል የጨመሩት ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ናቸው።

[2]«የሚያስረቀርቀው» ነበር የሚለው «ያ» ተሰርዝዋል። ተስረቀረቀ=የዘፈን ወይም የሙዚቃ ድምፅ መንቀጥቀጥ=quaver.

የዱር ኣውሬ ስማ ሲጨፍር ሲያስካካ።
ወፎች የሚሉትን ቋንቋዋንቻቸውን ልቀም
ዜማቸው በክራር በድምፅህ ይተርጎም።
ቢራቢሮዎቹ መልክትህን ይዘው
        ነፋስ ይውሰዳቸው።
ለሁሉም ያሰሙ የክራርን ዜማ
ሙዚቃን ለሚወድ ጥበብ ለተጠማ።
ዝፈን ይሰማሃል እንጨትና ዛፉ
ሳሮች ሲታጠፉ
        ቅጠሎች ሲረግፉ።
የሚንቀሳቀሱት ኣንተን ሲሰሙ ነው
ጩሀ ኣሞግሳቸው።
ዝፈን ይሰሙሃል መስማት የማይችሉት
የማይናገሩት፥ የማያስተውሉት፥
                የማይራቀቁት።
ኣስታዋሽ ኣታጣም
        ጆሮ የሌላቸው ልባቸው ተነክቶ
በገደል ማሚቶ።
ያስተጋቡልሃል
ዝፈን ይሰሙሃል!
የቅኔ እጀ ጠባብ ዜማ ኩታ ለብሰህ
ተጫወት እባክህ።
በምታውቀው ቋንቋዋ ተናገር ኣደራ
ስሜት ለመቀስቀስ መንፈስ ስታበራ።
ኣደራ ይገለጥ የሙዚቃው ቦታ
ይዳሰስ፥ ይጨበጥ፥ ድምፁ በፀጥታ።
ዝፈን ባለክራር፥

◆ 7/6/1950 የዛ.ኢ.

# ኣፅም

ማነህ የተኛኸው?
እንቅልፍ የደበተህ ስጋህን ጥለኸው
ምን ኖረሃል ኣንተ
        ንጉስ ኖረሃል ወይ
                ኖረሃል ወይ ጌታ
ወይ ቁርንጮ ለባሽ ለማኙ ከርታታ።
ሚኒስትር ደጃዝማች ወይም ፊታውራሪ
ባለብዙ ገንዘብ ኣሽከር ኣሳዳሪ።
ኖረሃል ወይ ኣንተ
ኣጥንትህ ወላልቆ እንዲህ የሻገተ።
ስራህ ምን ነበረ
        ቤትህ የት ነበረ
                ርስትህ የት ቀረ።
የተመራመረ ኣዋቂ ፈላስፋ
ብዙ መሰናክል ከኣለም ላይ ያጠፋ
ሳትሆን ኣልቀረኸም
ጉድ ነው መልክህ የለም።
ማነሽ ማነህ ኣንተ
ማናችሁ እናንተ።
ማነሽ በዘመንሽ የውበት እመቤት

ሆነሽ የገዛሽው የወንዶችን ጉልበት።
በክንድሽ ያለቀው
ወጣቱ ጎልማሳ የት ነው የወደቀው።
ምን ኖረሻል ኣንቺ ኣጥንትሽ ይናገር
እንጨት ተሸካሚ
ወይ ኲበት ለቃሚ
ወይ ልብስሽ ያደፈ ጥሬዋ ባላገር
ወይም ሸቅርቅርዋ እስቲ ተናገሪ
ሽቶሽ የጎረፈው መንጭቶ ከፓሪ።
በወርቅና ባልማዝ በሉል እንደሆነ
ተጫውተሽ የሄድሽው ስራሽ የገነነ
እስቲ ተናገሪ ቁዋሚ ያዳምጣል
ኣንቺ ለመሆንሽ ምስክርሽ የታል።
ያሻሃል ምስክር
ሞተህ ስትቀበር።
ድንጋይ ላይ ተፅፎ የሚናገርልህ
ሃውልት የሚያቆይህ፤
ዘመድ ያስፈልጋል ከሌላው ለይቶ
መንገደኛ እንዲያውቅህ ቆሞ ተመልክቶ፤
እንዲደነቅልህ ቀሪው ያንተ ስራ
ተነስ ኣንተው ጥራ።
እጎንህ ከተኙት ኣፅሞች በጉድጉዋድ
ኣለወይ ዘመድህ የምታውቀው ጉዋድ።
የታለ ኣባባ የታለች እማዬ
ጋሼ ወዴት ይሆን? የት ቀረች እትዬ።
ጠፍትዋል ምልክቱ
ኣጥንትና ስጋ ሲሰነባበቱ
ከሙታን ማህበር በመዝገብ ገብተሃል
እንደማንኛውም[1] ኣጥንት፥ ኣስከሬን ሆነሃል።
የሞት ጠባሳ ነህ ኣስተዋይ ስራውን
ከንቱ ነው የምትል ኣወይ ፍጡር መሆን።
የተንቀረፈፈው እጅ እግሩ ሸንበቆ
የተከፋፈለው ሰረሰሩ ወላልቆ።
ኣይኑ የወለቀ ጥርሱ ያገጠጠ
ጎድኑ ተቆጥሮ ጅማቱ ያለቀ።
የተገጣጠመ የስጋው ኣጥንት
ወዝ እንኩዋን የሌለው የሰው ምልክት[2]
ሆነህ የተኛኸው
የማትታወቀው
ምን ኖረሃል ኣንተ?

◆ 20/1/1949

# ኣሞራና ቅል ተጋቡና

ኣሞራና ቅል ተጋቡና . . .
እንጉዋዝ ኣሉና «ውጫገር» ለማየት
እንጉዋዝ ኣሉና ጥበብ[3] ለመገብየት

---

[1]«ማንኛውም» ነበር የተፃፈው።
[2]«ወዝ የሌለው የሰው ዘር ምልክት» ነበር ስንኙ የሚለው። «እንኩዋን» የሚለው ቃል በእጅ የገባ ወሽመጥ ሲሆን፥ «ዘር» የሚለውን ቃል ያስወጣሁት እኔ ነኝ። «ዘር» መውጣቱ የስንኙን ትርጉም ኣይለውጠውም። ግን፥ የ«ዘር» መውጣት፥ ቤት መምቻውን «ት»ን እንድንረግጠው ስለሚያስገድደን ስንኙ ከጎረቤቱ ጋር ይገጥማል።
[3]«ጥበብን» ነበር የሚለው።

እንጉዋዝ ኣሉና እንሻገር ባህር
እንጉዋዝ ኣሉና ይሻላል መሞከር
ያገር ልጆች ለፉ፥
ያገር ልጆች ሰሩ
ሄዱና በረሩ
ባህርም ተሻገሩ።
ሄዱ ቀላወጡ
የጥበብ ሰናፍጭ በርበሬና ወጡ
ኣይቀር ሆድ መቁረጡ።
በጥላቻው ብዛት
በመገፋት ብዛት
በግልምጫው ብዛት
በተንኮሉ ብዛት
በፉክክር ብዛት
በፉክክር ብዛት
በምቀኝነት
በፈረንጆች እውቀት. . .
ያገር ልጆች ለፉ እያቀረቀሩ
ያገር ልጆች ኣዩ
ፈለጉ ሞከሩ
ያገር ልጆች ሰሩ
ኣዳመጡ ሰሙ
በጥበብ ኣዋራ በሽታ ህመሙ
ሁሉም ተዳከሙ።
መስልዋቸው ውጫገር ነፍስ የሚዘራበት
ሰው ሞቶ በስብሶ ኣድጎ ሚያብብበት
መስልዋቸው ኣውሮጳ የነፃነት ኣገር
የሚችል መስልዋቸው ሰው ሁሉን መናገር
መስልዋቸው ኣውሮጳ ያኛው ሌላ ገነት
ኣዳም ከሄዋን ጋር የሚጫወትበት
እንየው ኣሉና
መስልዋቸው ኣውሮጳ ፍፁም የሉል[1] ኣገር
ሰው እንደሰው ሁሉ ሲሄድ የሚያምርበት[2]
[ ] ቅበት[2]
ሰው ኣንድ ዘር የሚሆንበት[2]
ትልቅ ዲሞክራሲ፥
ሰው ከቤቱ ሆኖ ዳቦ ሚበላበት
ህግን ተከትሎ የሚሰደብበት
የሚዛረፍበት
የሚጋደልበት
ትልቅ ዲሞክራሲ
እንየው ኣሉና
ያገር ልጆች ጉዋጉ
ያገር ልጆች ሄዱ
እጀ ጠባብ ኩታ ጥብቆም ወሰዱ
ያገር ልብስ ያኮራል
ከሌላው ለይቶ ምስክር ይሆናል
ያገር ልጆች ኮሩ፥ ከዘራ ጨበጡ
ጥበብን ለበሱ፥ ለመንሸርሸር ወጡ።
ሰው ያያል ምን ጊዜም
«ኣይን ወረተኛ ነው ይወዳል እንግዳ»
ኣዩ ፈረንጆቹ
ተቹ ፈረንጆቹ

[1]በደንብ ኣይነበብም።
[2]ጨርሶ ኣይነበብም።

ያገር ልጆች ለፉ
ያገር ልጆች ሰሩ፤
ምን ይሆን ኣሉና
ምን ይሆን በማለት በወዲያኛው ኣለም
ኣዳም የሚፈጥረው የኛ ኣገር ሲጨልም
ምን ይሆን ምትሃቱ
ምን ይሆን እውቀቱ
ሌላውን ለውጦ መልኣክ ያደረገው
ምን ይሆን ቅመሙ ፈረንጅ የፈጠረው
ምን ይሆን ኣቶሙ እንዲህ የረቀቀው?
ብዙ ሺህ ዘመናት እኛ ሳናገኘው
ምን ይሆን ኣሉና
እንደ ጥሩነቱ መጠየቅ መጥፎ ነው
እውነቱን ሲገልጠው
እውነቱን ሲያፈርጠው
ምሳሌውም ይላል
«ኣጥብቆ ጠያቂ የናት ሞ ት ይርረዳል»
በነጭና ጥቁር
እንዳገሩ ሁሉ
ከስር መሰረቱ
ከተፈጥሮ እድገቱ
እርግጥ ይኖር ይሆን መለያየት ባንጎል?
ከጥቁር ጭንቅላት እርግጥ የነጭ ራስ
እውነት ኖሮት ይሆን ሌላ ልዩ ህዋስ?
ከሻንቅላው ጦጣ
ፈረንጁ ዝንጀሮ
ምን ይሆን መተቱ የበላው ቆፍሮ
የሰማይ መሬትን ጥበብ ያሳወቀው
ምን ይሆን ምስጢሩ ፈልጎ ያገኘው
ምን ይሆን ፈረንጆች ብረት ኣገጣጥመው
ኮከብ የሚቃኙት በጠፈር ውስጥ ሄደው[1]
ምንድን ነው ቅሽጣ . . . . ያ[2]
ተደንቆ ያለው . . . . . ጨ[2]
ምንድነው ቀለሙ
ምንድነው መስመሩ
ምንድነው ዝገቱ
ምንድንነው ኣዘቅቱ
ምንድነው ኣዋራው ጢሱና ብናኙ[3]
ከኛ ውጪ ያለው
እኛ ያላየነው እኛ ያላወቅነው
ምን ይሆን ኣሉና
ሄዱ ተዳከሙ ለማግኘት ምስጢር[4]
ጭንቅላት እስኪዞር
ኣንገት እስኪሰበር
ኣይን ኣብጦ እስኪሙዋሙዋ[5]

ቤተ መፃህፍትን እያመሳከሩ
ጠየቁ መለሱ
መለሱ ጠየቁ
እንደዚህ ኖርዋል ወይ! ብለው ኣደነቁ
ታዲያ ምኑ ኖርዋል የቱ ነው ኣዲሱ
እኛው ኣገር ኣለ ጂኒው መሃንዲሱ

---

[1]«በጠፈር ውስጥ» ግምት ነው ኣይነበብም።
[2]ጨርሶ ኣይነበብም።
[3]«ብናኙ» የሚለው ግምት ነው የተፃፈው «ብ» ብቻ ነው።
[4]«ምስጢሩን» ነበር የሚለው። እንዲገጥም ተቀይርዋል።
[5]ከዚህ ስንኝ በሁዋላ ጨርሶ የማይነበቡ ኣንድ ወይም ሁለት መስመሮች ኣሉ።

ምሶሶውን ተክሎ ጣራ ሚያዋቅረው
ድንጋይ እያጋጨ እሳት የሚፈጥረው
እኛም ኣገር ኣለ!
እንዴ!
        እኛም ኣገር ኣለ ጋኔን የሚስበው
ኣተላ እየበላ የሚለፈልፈው[1]
እኛም ኣገር ኣለ ጂኒ መተተኛው
ኣንደርቢ ልኮ ቤት የሚያቃጥለው
የቱ ነው ኣዲሱ![2]
        የቱ ነው ምስጢሩ ኣሉና ጠየቁ
ጥበብ ሲሄዱበት እንደመደበቁ
        ጥበብ ሲጨብጡት እንደማሙዋለጩ
        እንደሚያፈራርስ ሳያውቁት ሲጋጩ
ጥበብን ሲያጎሉት[3] እንደመሰወሩ
ቆፍረው ሲያወጡት እንደመቀበሩ
        ኣልቁዋል ተስተካክልዋል ብለው ሲፈፅሙት
        ኣዲስ እንደሚሆን ገና እንዳልጀመሩት
ተጣርቶ ሲቀመጥ እንደመደፍረሱ
እሳቱ ሲዳፈን ደግሞ እንደመጨሱ
«ታዲያ የቱ ኖርዋል?»
ኣሉና ጠየቁ፥ ምንድነው ምትሃቱ
ጥበብ ሲያፈጡበት ኣይን እንደማጥፋቱ
ጥበብ ሲጠይቁት መልሶ በተራው
ጭንቅላት እንዲዞር[4] የሚነዘንዘው[5]
ኣሉና ጠየቁ
        «የቱ ነው ኣዲሱ?»
ጥበብ ሲከተሉት እንደመገስገሱ
ጥያቄ ተባዛ
ጥያቄ ተናዛ
ሰበብ ተፈጠረ
ሰበብ ተከመረ
ጥያቄን ኣርግዞ ጥያቄ ወለደ
ጥያቄው ጥያቄ፥ ጥያቄው ጥያቄ
        ማለቂያ የሌለው
        ነጥብ የማይገታው
ይሆንና ባዶ ወደመጨረሻው[6]
ጥበብን ሰባብሮ
        ሲሄድ ሃሳብ በሮ
ለካስ እንዲህ ኖርዋል!

◆

# ይራመዳል ገና

ወዴት ኣለ እንቅፋት
ለዚህ ትንሽ ተባይ
        መሬትን ኣስጊጦ ላደረጋት ገነት።

---

[1]«የሚስለፈልፈው» ነበር የሚለው።
[2]ይህ ግጥም ሁለት ቦታ ተፅፎ ይገኛል። ከዚህ ስንኝ በታች ያሉት ስንኞች «የቱ ነው ኣዱሱ» በሚል ርእስ ስር ተፅፈዋል። የገልባጭ ስህተት እንደሆነ ያስታውቃል።
[3]=ጉልህ ሲያደርጉት።
[4]ኣንደኛው ቅጅ ላይ «እንዲያዞር» ነበር የሚለው።
[5]«ለሚነዘንዘው» ነበር የሚለው።
[6]ይሄ ስንኝ «የቱ ነው ኣዲሱ» የሚለው ግጥም ውስጥ የለም።

ባራት እግሩ ሲሄድ ባለም ላይ ገንፍሎ
ሲንፍዋቀቅ ሲጎተት ሁዋላም ብድግ ብሎ
ኣንጎሉ ረቀቀ፥
ማድረግ መፍጠር ቻለ፥ እየተናነቀ።
በስራው ኣደገ፥ በኣእምሮው ኣደገ
በሃሳቡ ኣደገ።
ዘልቆ እየጠለቀ በመመራመሩ
ለውጥ እየፈለገ በመከራከሩ
ሁሉንም በለጠ
ሁሉንም ጨበጠ፤
የጥበብ እንቁላል ኣስኩዋሉ ፈረጠ
ቅርፊቱ ተሰብሮ ዛፉ ተመጠጠ፤
ምስጢር ተገለጠ።
የባህር ሆድ እቃው ወጣ ተበዝብዞ
ሰማይ ተሰንጥቆ
እውቀትና ጥበብ በብልሃት ተይዞ።
የመሬት የውስጡ የስር የባህሉ
ኣካባቢው ሁሉ
ተጠና ታወቀ ሃይል እየተሰፋፋ
ጉልበት ተከማቸ መሰናክል ጠፋ።
ኣቶም ተነቆረ
ኣየር መጋረጃው በሰው ተበገረ።
መች እንዲህ ሆነና
ይለመዳል ገና፥
ከተማውን ሰርቶ ይኖራል በሰማይ
ባዶ ቦታ ሄዶ ይዘረጋል ድልድይ
የስልኩ ማዞሪያ «ኣሎ! ጨረቃ!» ነው
ቁርስ ከማርስ ላይ፥ ከቬነስ ላይ ምሳው
ከመሬት እራቱን
በልቶ ይጨፍራል ሜርኩሪ ላይ ዳንሱን።
የብርሃንን[1] ፍጥነት ሲሽቀዳደም ይዞ
ከመቅፀበተ[2] ኣይን ይሄዳል ተጉዞ።
ያንዱ ኮከብ መቅናት[3] ለሌላው መረጃ
ሆኖ መራመጃ
ኣየርን ይተዋል ሲፋጠን ወደ ላይ
ኣለማት ተገዝተው ይጠበዋል ሰማይ።
ሁሉን ይለውጣል
ለማየት ለመስማት ለማሽተት ለመንካት
ለጣም ኣዲስ ኣይነት
ስያሜ መጠሪያ መንገድ ይሰጠዋል።
ባዶ ቦታ ሁኖ ፈጥሮ መገናኛ
በሲኮንድ መቶኛ
ሁሉንም ይሰራል።
የጥበብ ምእራፍ ኣዳዲስ[4] ይሆናል።
የፀሃይን ፀሃይ፥ የፀሃይን ፀሃይ፥
ይኸ ትንሽ ተባይ
በስልጣኑ ገዝቶ ያስገብራቸዋል
መሬት ስታበራ በጨረቃ ዛፍ ስር
ይፈጥራል ሙዚቃ ቅኔ ሲደረድር።

---

[1]«የብርሃን» ነበር የሚለው።
[2]«ከመቅጽበት» ነበር የተጻፈው። በእጅ የተፃፈ እርማት «ከመቅፀበተ?» ይላል።
[3]=ኣገር ማቅናት፥ ማልማት።
[4]«ዳ» ኣይታይም።

ያገኛል መድሃኒት
ሲኖር በከዋክብት[1]
ሞትን ያሸንፋል
ሁሉን ሲቆጣጠር እግዚኣብሄር ይሆናል።
ወዴት ኣለ እንቅፋት
        የት ኣለና ዳገት
ለዚህ ትንሽ ተባይ
        ገና ይራመዳል፤
                ይራመዳል ገና።[1]

◆

# የሞት ኣለም ሞት

ሰው፥ ሰው፥ መሆኑን . . .
ሰው ሰው መሆኑን፥ የማያሳውቅ ከሆነ በጭካኔ ሞት
ኦ መሬት ስጠኝ እስከዘላለም ሞት የሞት
ሞት ምን የህልፈት ኣለም ኣለም ጥሩንባ–ምን የጥፋት ከበሮ
ምራ የክፋት ወጥመድ የቀጋ ሾህ ኣለምን በሙሉ ኣስሮ
ምን ጩኸት ያሰማናል በየደቂቃው እርምጃ
ያቶሚክ ቦምብ ያዳፍኔ . . .
        የተወሳሰበ ሙዚቃ ድምፅ የመትረየስ ወይ የጠመንጃ
የተጠላለፈ ህይወት ሃረግ የመሰሪነት ስጋጃ
ምን የመርዝ የጠብ ጭንቅላት
የገበሎ ራስ ናዜራ፥ የፋኘት ምራቅ ነቀርሳ
ምን ስራ ስር ያረግ ሬሳ
ምን የምድር እምብዋይ የጠጅ ኣሸር
                        የድፍድፍ ኣንቃር ያተላ
ምን የደሃ እርሾ ኮምጣጤ የሚንተከተክ የሚፈላ
ዋጊኖስ[2] እፀ ዘዌ[3]፥ የፍልፈል ኣፈር ፍልፈላ
ያንዱ ሞት የሌላ ህይወት . . .
ያንዱ መኖር ለሌላው መጥፊያ።
ጥሩ ሙዚቃ ጥሩ ሙዚቃ ግሩም ማለፊያ፥
ግሩም ማለፊያ
ኣቤት እግዚኦ፥ ኣቤት
ቪየትናም የቪየትናም እልቂት
ናጋሳኪ የሂሮሽማ መጥፋት
ሻርፕቪል–ሞት የሞት ሞት
        የሬሳ ክምር መኣት
የሰው ልጅ ጥፋት መቃብር
                የሰው ልጅ መኖር ወይ ኣለመኖር
የሰው ክፋት ትል የማይሞት፥
                የሰው ተንኮል መርዝ የማይበገር
ጥቁር ቀይ፥ ቀይ ጥቁር
ድብልቅልቅ ውጥንቅጥ
ከሰማይ በታች ከመሬት በላይ፤
                ያንዱ ሞት የሌላው ህይወት

---

[1]በእጅ የተፃፈና የተጨመረ ስንኝ ነው።
[2]«ዋጊ ኖስ» ነበር የተፃፈው። መዝገበ ቃላቱ ግን «ዋጊኖስ» ይላል። ዋጊኖስ=የተቅማጥ መድሃኒት የሚሆን ተክል።
[3]«እዳ ዘዌ» ነበር የተፃፈው። መዝገበ ቃላት ውስጥ ግን ኣላገኘሁትም። ዘዌ=ወፎች የሚበሉት፥ ወይን የሚመስል ፍሬ ያለው ተክል፥ ይልና «እፀ ዘዌ» የሚል ምሳሌ ይሰጣል።

በግ ይታረዳል፥ ሰንጋ ይጣላል፥ የሰርግ ድግስ እልልታ
የፆም ጠጅ መርዝ ስካር፥ ካንቺ ሙዚቃ ኩዋኩዋታ
ኣታሞ፥ ያለም መሽከርከር፥ ከንቱ የሌላው ኣለም ኣለም
ትቢያ የትቢያ ትቢያ - ኢምንት - ቅንጣት ስውር ፍፁም
ህይወት ኣበባ ፅጌረዳ፥
                ብርሃን ጭላንጭል ፍንጣቂ
የሞት እስትንፋስ ጠፊ፥ ረቂቅ የሰባራ ገል ድቃቂ
ኣለም ሆይ ሂጂ ጥፊ፥ ሂጂ መጥፎ ክፉ ኣለም
እንግዳ መሆኑን ያላወቀ፥ እንግዳ መሆኑን ያጣው የለም
ኣለም ዘላለም በሰው ዘንድ
                ከንቱ ነው ህይወት ዘላለም።
የቴወድሮስ ሞት መስዋእትነት
        ኣብርሃም ሊንከን፥ ማርቲን ሉተር ኪንግ፥ ማህትማ ጋንዲ
ኬኔዲ ደግሞ ኬኔዲ
ብዙ ሰማእታት ጠፍተው የቀሩት
ብዙ ሰውነት ማሰብ የሞቱት።[1]
ኦ ምን ድምፅ ያሰማናል
        ምን የጉግ ማንጉግ ጩኸት ጋጋኖ
ምን የምናምን ምናምን ሙዋርተኛ ደንቃራ ሆኖ
ምን የፍልፈል ኣፈር ፍልፈላ፥
        ምን የመቃብር ኣፈር ትኩስ -
                የሙት ኣማጣኝ መንፈስ ሳቢ
የቤት ጥቀርሻ ጢስ ጥላሸት፥ የምሰሶ እድፍ እጣቢ
ምን የሰው ክፋት መሰሪነት የሰው እርጉምነት ኣንደርቢ
ምን የሃሳብ ቅንቅን ስራይ[2] የህይወት ጥንጣን[3] ነቀዝ
ምን ክፋት የኑሮ ወረት፥ የሰው ልጅ እንጠረፋ[4] መሬንዝ[5]
ኖጊኖስ[6] እፀ ዘዌ[7]
        የለቅሶ ኣስክሬን ዝንብ ሬሳ፥ የሽረሪት ድር ሳቅ ተከናንቦ
ያለም መጠን ያለም መውዘግዘግ እምሃበ ኣልቦ ሃበ ኣልቦ
ምን የጉግ ማንጉግ ጫጩት ጋጋኖ፥
                ምን የህልፈተ[8] ኣለም ጥሩንባ
ምን የሰው ሃዘን የሰው ጩኸት፥
                ምን ያዳም ልጅ ዘር፥ የደም እንባ።

◆

# ከሞቱት ቆይትዋል

ከሞቱት ቆይትዋል ብዙ ዘመን ሁንዋል
        ብዙ ነበር ጊዜው
ግን ፎቶግራፍዋ[9]፥ ደብዳቤዋም ኣለ
        በጠጉርዋ ጉንጉን የጠቀለለችው

---

[1]ምን ማለት ይሆን? ትርጉሙ ኣልገባኝም።
[2]ኣለቃ ዋና - principal። ግን እሱም ቢሆን «ሰራይ» ነው እንጂ «ስራይ» ኣይደለም።
[3]ጥንጣን=እንጨት የሚሰረስር ትል።
[4]«እንጠረፋ» የሚል ቃል ኣላገኘሁም።
[5]«መሬንዛ» ሳይሆን «መሬንዝ» ይመስለኛል። ኣንደኛ ይገጥማል፤ ሁለተኛ «መሬንዛ» መዝገበ ቃላት ውስጥ የለም። መሬንዝ=መርዛማ ፍሬ ያለው ተክል።
[6]«ዋጊ ኖስ» ነበር የተፃፈው። መዝገበ ቃላቱ ግን «ዋጊኖስ» ይላል። ዋጊኖስ=የተቅማጥ መድሃኒት የሚሆን ተክል።
[7]«እዳ ዘዌ» ነበር የተፃፈው። መዝገበ ቃላት ውስጥ ግን ኣላገኘሁትም። ዘዌ=ወፎች የሚበሉት፥ ወይን የሚመስል ፍሬ ያለው ተክል፥ ይልና «እፀ ዘዌ» የሚል ምሳሌ ይሰጣል።
[8]«የህልፈት» ነበር የሚለው፥ በእጅ ፅሁፍ ታርምዋል።
[9]«ግን ፎቶግራፍዋ ኣለ፥ ደብዳቤዋም ኣለ» ነበር ስንኙ የሚለው። የመጀመሪያው «ኣለ» ባይኖር ይሻላል።

ምን ቀነ[1] ቀጠሮ ነው
ቀን የቀን ጐደሎ
የቀን ጥቁር መጥፎ።
ኣበባ ሄድኩ ይገፎ . . .
እዚያ ኣበባ ኣልጠፋም
በመቃብርዋ ውስጥ ኣበባ ተኝትዋል።
ስሜቴ ፈነዳ ገላዬን በተነው
ነፍሴን ነቀነቃት
እንባዬ ወረደ ጉንጬን ኣረጠበው
ለተረሳ ነገር እንዴት ያለቅሳል ሰው!
ለተረሳ ነገር
ምን ጊዜው ቢረዝም . . .
የዚህ ኣለም ጣጣ እያንከራተተኝ
የዚህ ኣለም ስቃይ እየቦረቦረኝ -
ሲጨንቀኝ ሰውነት
ፍቅሬ ይሁን ያንቺ የኔ መቃብር ቤት፤
ህይወት ነዶ ጠፍቶ ሞት ፍሙን ሲያዳፍን
ያን ጨለማ ጉዋዳ ሄጄ ልተኛበት።
ይመስላል ዘላለም . . .
የወደዱትን ሰው[2] ኣይን ኣይኑን ሲያዩት
ይመስላል ዘላለም ኣድማስ ኣልፎ ኣድማስ፤
ምጥቀት ኣልፎ ምጥቀት፥ ጠፈር ኣልፎ ጠፈር
ይመስላል ዘላለም ሰው ባካል የሚኖር።
ድሮ ኣውቀዋለሁ፤
ተረድቼዋለሁ፤
ፀሃይ ጥቁር ስትሆን
ቀን ቀንን ሲያጠላው ሌት ሌትን ሲሸፍን
እረስቼው እንደሁ።
እንዴት ኣንቺን ልርሳ፥
ነፍሴ ኣብርዋት የሚኖር የፍቅርሽ ጠባሳ።
«ፍቅርሽና ፍቅሬ የተወሳሰበው
ኣልበጠስ ኣለኝ ብሰበው ባሰበው»
ማ ነበር . . . ማ ነበር
ማ ነበር እንደዚህ፥ ብሎ የገጠመው?
ይመስላል ዘላለም
ኣንች የኔ እመቤት ብያት የነበረ[3]
ኣንተ የኔ ጌታ
ኣንተ የኔ ጌታ ብላኝ የነበረ
ኣንቺ የኔ እመቤት
ይመስላል ዘላለም።
እንባዬ ወረደ፥ ልቤን ኣቃጠለው፥ ልቤ ተነደለ
የሰቀቀን እሳት ኣካሌን ሲያነደው ደሜ ገነፈለ
የደም ጥቁር እንባ . . .
የቅጠል ጭማቂ ኣረንጉዋዴ ኣበባ
የደም ጥቁር እንባ
ቆዳ የሚያሳርር መንፈስ የሚያባባ
ኣልቀሰቅሳትም . . .

---

[1]ከ «ቀነ» ይልቅ «ያል» ቢሆን ይሻል ይመስለኛል። ወይም ደግሞ የቃሎቹ ኣደራደር እንደሚከተለው ቢለዋወጥ ለማንበብ ይቀላል። «ምን ቀነ ቀጠሮ፥ ቀን የቀን ጎዶሎ፥ ጥቁር መጥፎ ቀን ነው።»

[2]«ሰው ሰውን ሲወዳት ኣይን ኣይኑን ሲያዩት» ወይም በእጅ ታርሞ እንደተፃፈው «ሰው ሰውን ሲወዱት ኣይን ኣይኑን ሲያዩት» ኣገባቡ የሰዋስውን ህግ የተከተለ ስላልመሰለኝ ቀይሬዋለሁ። ምናልባት፥ «ሰው ሰውን ሲወዳት ኣይን ኣይንዋን ሲያያት» ማለትም ይቻል ይሆናል።

[3]እዚህ ቤት ውስጥ፥ ተያቢዎች ትርፍ ስንኞችን ያስገቡ ይመስላል። ምናልባት፥ «ኣንች የኔ እመቤት ብያት የነበረ፤ ኣንተ የኔ ጌታ ብላኝ የነበረ፤ ይመስላል ዘላለም . . . » ሳይሆን ኣይቀርም።

ቡዳ እስዋን ኣይበላም ቢስ እስዋን ኣያይም
ኣልቀሰቅሳትም በነፍሴ ተጉዤ እጠይቃታለሁ
ኣውቃለሁ ኣውቃለሁ
ኣለ ትዝታዋ . . .
ኣውቃለሁ - ኣውቃለሁ
በመቃብርዋ ውስጥ ጢስ እንጨት ይጨሳል
ከርቤ፥ ብርጉድ፥ እጣን . . .
መቃብርዋ ሽቱ
ጣፋጭ መኣዛ ኣለው ኣጥንትዋ ታቦቱ
መቅደስ ቤተልሄም ቅኔ ማህሌትዋ . . .
እጣኑ ይጨሳል ይታጠናል ቤትዋ
ፍቅሬ ሙሽራዬ
እመቤቴ ፍቅሬ ያለም ኣለኝታዬ
ኣቴትዋ ይታጠናል
ልዩ መኣዛ ኣላት ማግሪፍ፥ ዲዩር፥ ሻናል
በመቃብርዋ ውስጥ ጢስ እንጨት ይጨሳል
በመቃብርዋ ውስጥ ኣበባ ተኝትዋል
ፍቅሬ ፍቅሬ ፍቅሬ፥ ፍቅሬ ፍቅሬ ፍቅሬ
እመቤቴ ፍቅሬ እመቤቴ ፍቅሬ፥ እመቤቴ ፍቅሬ እመቤቴ ፍቅሬ
ፍቅሬ ሙሽራዬ ፍቅሬ ሙሽራዬ፥ ፍቅሬ ሙሽራዬ ፍቅሬ ሙሽራዬ
ፍቅሬ ኣለኝታዬ ፍቅሬ ኣለኝታዬ፥ ፍቅሬ ኣለኝታዬ ፍቅሬ ኣለኝታዬ
እንባዬ ወረደ . . .
እንግዲህ ይበቃል - ይቅር፥ ይቅር - ይብቃ
በድካም - መድከም፥ ባሳብ ሃሳብ ኣለ
ባዘን . . . ሃዘን . . . ሃዘን . . .

◆

# ከበሮ

ኣለው ሃያል ግርማ
ኣለው፥ ኣለው፥ ኣለው
ኣለው ሃያል ግርማ
ይቀሰቅሰኛል ጩኸቱን ስሰማ።
በሰውነቴ ላይ ይፈጥራል ሽብር[1]
ኣለው መስተፋቅር
ኣለው መስተፋቅር።
መድፍ የተተኮሰ
እሳተ ገሞ ራ[2] ገንፍሎ የጨሰ
መብረቅ የወረደ
ገደል የተናደ፥
ማእበል ነጎድጉዋድ መስሎኝ እቀራለሁ፤
እደነግጣለሁ።
ያንዘፈዝፈኛል እንዳዶ ከብሬ[3]
እጄ ሲርበተበት ይጨፍራል እግሬ
የሰርግ ኣዳማቂ፥ ነው ኣዶ[4] ወሸባ
ሙሽራ ሲያባባ[5]

---

[1]«መሸበር» ነበር የሚለው።
[2]«ጎመራ» ነበር የሚለው።
[3]«እንዳዶከብሬ» ነበር የሚለው። መዝገበ ቃላቱ፥ ኣዶ ከብሬ፥ ኣዶ ከበሬ፥ ኣዶ ከቢሬ እያሉ በሶስት ኣይነት ጽፈውታል።
[4]የተፃፈው «ኣዮ» ነበር። ግን «ኣዮ ወሸባ» የሚል ኣላገኘሁም። ያለው፥ «ጉሮ ወሸባ» ወይም «ኣዶ ወሸባ» ነው። ዘፈኑም የሚዘፈነው ለኣዳኝ እንጂ ለሰርግ ኣይደለም። ግን፥ በኛ ዘመን «ኣደን ወጣሁ» ሲባል «ሴት ፍለጋ ሄጄ ነበር» ማለት ነበርና፥ ጋብቻን እንደግዳይ ቆጥረውት ይሆናል።
[5]«ሲያባባ ገባ» ነበር የሚለው። ኣራሚዎችም «ሲያገባ» ብለው ፅፈውበታል።

በጩኸት ኩዋኩዋታ ድልቅ ድልቅ ብሎ
ሰው የሚያተራምስ ስካር ኣስከትሎ።
ሃዘን መቃብር ፀሎትና ፍትሃት
የሚመታው ደረት
ያልቃሾቹ ስሜት
ይጠራል ከጉድጉዋድ ሄዶ የጠፋውን
ባፈርና ድንጋይ ሲጎሸም ሳጥኑን።
የቤተክርስቲያን የሃይማኖት ፍቅር
የሽኮች ድቤ ነው ያምልኮት መደብር።
ያመጣል ሁካታ የጥምቀት ጭፋሮ
ከበሮ ከበሮ፤
ያመጣል ጎትቶ ልጃገረዶቹን
እንቁጣጣሽ ብለው የሚጨፍሩትን፤
ያመጣል ከጫካ ጎበዞቹን ይዞ
ጦር እየሰበቀ ጎራዴውን መዞ
ድምፅ ነው የሰሙት
ወይም[1] የጦርነት
ያረመኔ ጥሪ ተነሳ ታጠቅ
ጠላት መጥቶብሃል ቀስትህን ኣርቅ።
የፈረሱ ኮቴ ሽምጡ ሶምሶማ
ኣብዋራ ሲያስነሳ ድምፁን የሚያሰማ፤
ናዳው ሲንከባለል በጩኸት ደረጃ
መሬት የሚያናጋ ሰልፍ ነው እርምጃ።
ጊዜን የሚለካ፥
ሰኣት እየለየ ሲጠፋ ሲተካ፥
የሙዚቃው ውሉ ማሰሪያው ሽምቀቆ፥
ባይጮህ እንኩዋን ኣለ ከስር ተደብቆ።
የሚያስተጋባ ነው ዜማው ተሰብስቦ
ሁላ[2] ሁኖ ሮክ ኤንድ ሮል
ቻቻ ቡጊ ቡጊ ዘመናዊ ማምቦ።
ዛር ነው ውዝዋዜ፤
እብደት ነው ትካዜ፤
ያካል ንቅናቄ ኣገሩ ሙዚቃ
ሰው ያሽከረክራል፥ መንፈስ እያነቃ።
ኣቁዋርጦ ይመጣል ሲሮጥ ከሩቅ ኣገር
ቤቴን ለመበዝበዝ፥
ልቤን ለማሸበር፥
ልቤን ለማሸበር . . .
ከበሮ
ከበሮ።

◆

# በባእድ ሃገር

ቦታው ነበር ትልቅ፥ ትልቅ፥ ትልቅ በረት
እንሰሳት ኣራዊት የሚጫወቱበት።

---

[1] «ወይም» የሚያማርጠው ነገር የለም። «ያውም» ሳይሻል ኣይቀርም።
[2] «ሁሉ»?

ቦታው ነበር ፈረንጅ የሚስማራበት
ለማየት ትንግርቱን ኣዳዲሱን ነገር —
        ትል ወፍ እባብ ሆኖ፥
                ባራት እግሩ ሄዶ፥
                        ዝንጀሮ ላይ ሲደርስ ሰው ሰው የሆነበት።
ወጣቱ ስፍራውን ዞሮ[1] ባይኑ ቃኘው
ወጥመዱን ጎበኘው።
ዝንጀሮ ነበረ፤ ቁጭ ብድግ እያለ
ወደሱ እየሮጠ መጣና ዘለለ
ሳቀ ተጫወተ።
ከሌሎች መርጦ ኣተኩሮ ቢያየው
እግዚኣብሄር ይይለት ዝንጀሮ መሰለው?
እንደሰረቀ ሰው ኣደባባይ ማህል
ነጮቹም ኣፍጥጠው ይመለከቱታል።
ፍንክች ያበሻው ልጅ፥ ወይ ኣይኑ ሊሰበር
እሱም ኣተኩሮ ይመለከት ጀመር።
ኣተኩረው ሲያዩት፥ ኣሳማ - ኣይጥ መሳይ፥ ነብርም[2] ድመት ነው።
እባብ ዘንዶ ቢሆን፥ ፍጥረት ተመሳሳይ፥ ምን ጊዜም ኣለው[3]።
ኣያቸው ነጮቹን፥ ሁሉም ኣፈጠጡ
የፈሩ ይመስል በርግገው ሊወጡ።
ልቡን[4] ሳቅ ኣፈነው
ኣየ[5] ተመልሶ፥
        ገረመው፥ ደነቀው።
የህይወት ቆሻሻ፥ የህይወት ጭቅቅት
ሰውን ሰው ለመብለጥ[6]፥ ሲለፋ ሲራኮት
ኣንዱ ባንዱ ሲስቅ
ያኛው ያንን ሲንቅ
«መኖር ኣለመኖር» ሼክስፒር እንዳለው
መብለጥ ወይ መበለጥ፥ ጥያቄው ይኸው ነው።
መግዛት
ወይ መገዛት
ወይ ችሎታን ማመን
ችሎታን ማሳመን
ወይ መሄድ በሰማይ
ወይ እንደትሎቹ መቆጠብ መሬት ላይ
ወይም[7] እንደሙታን
መተኛት ሳይፈሩ ተከናንቦ ኣፈሩን።
ገረመው፥
ደነቀው፤
ሰው ኣፈር ነበረ
ሰው ሸክላ ነበረ

---

[1]«ዞር ብሎ» የሚለው በእጅ ፅሁፍ ታርምዋል።
[2]«ነብርም» የሚለው ቃል በትክክል ካልተነበበ ይሄ ስንኝ የማይገጥም ይመስላል። «ነብርም» ብለን እንደ ሶስት ቀለም ሳይሆን፥ «ነብርም» ብለን እንደ ሁለት ቀለም ካነበብነው፥ ያዳንነውን ቀለም ቤት መምቻውን «ው»ን እንረግጥበታለን። ጎረቤት ስንኙ የሚያልቅበት ቃል «ኣለው» ቤት መምቻው የተረገጠ «ው» ስለሆነ፥ ሁለቱ ስንኞች ቤት እንዲመቱ (እንዲገጥሙ) እናስገድዳቸዋለን።
[3]«ፍጥረት ተመሳሳይ ምን ጊዜም ኣለው» የሚለው ሃረግ፥ ሃሳቡ ቢገባኝም ስህተት ያለበት መስሎኝ ነበር። ኣራሚዎች ለማስተካከል የፃፉትን ስመለከት ችግሩ የኔ ብቻ ኣለመሆኑ ስለገባኝ ነው ይህንን ማስታወሻ የፃፍኩት። ሃረጉ፥ «ኣንድን ፍጥረት የሚመስል ሌላ ፍጡር፥ ምን ጊዜም ማግኘት ይቻላል» ነው የሚለው።
[4]«ልቡንም» ነበር የሚለው፤ «ም»ን ኣራሚዎች ሰርዘውታል።
[5]ኣየ=ተመለከተ (ኣይየ)።
[6]«ለመብለጥ ሲል» ነበር የተፃፈው። «ሲል»ን ኣራሚዎች ሰርዘውታል።
[7]«ወይ» ነበር የሚለው፤ ኣራሚዎች «ወይም» ብለውታል።

ሰው የሚንቀሳቀስ መኪና ሆነ ሰው . . .[1]
ሆነ ዝንጀሮ፥
መሆን ኣይነት ብዛት፥
መሆን ምስጢር ኣለው።
ነበረው በኣገሩ፥ ሰው ነኝ የሚል እምነት
እሱም እንደሌላው ሲያስብ ያደገበት
ነጮቹ ኣፈጠጡ
ያቃጥለው ጀመር ሲቃ፤ ኣይኖቹ ጎረጡ[2]፥
የተሞጫሞጨው የተመቸ ብሩ ኣገር ያፍሪቃ ቃጠሎ[3]
ኣይኑ ነበር እሳት – የእሳት ኣሎሎ፤
ባይኑ ገላመጠ
ባይኑ ኣስደነገጠ
ኣይናቸውን ኣፍረው ሲያቀረቅሩ
በወጣት ህሊና ሊመረምሩ
ኣይኑ[4] ኣልተሰበረም ኣይናቸው ተሰብሮ
ፊታቸውም[5] ዞሮ . . .
ሰጡ ጀርባቸውን
ሁሉም እያፈሩ ሲለቁ ቦታውን[6]
ኣሮጊት ጎፍጣጣ
እመቤት ሞንዳላ፥ ዳሌዋ የወጣ፥
ግዴለሽ ጎረምሳ፥ ሽማግሌው ሁሉ
ኣማቱን፥ ኣማቷን
የታባታቸውን።
ጀርባቸውን ሰጡ፤
መንፈሱ ዘመረ፤
«ድል ነው» ኣለ፤ «ድል ነው»
ወገን ዘር ኣይደለም
እውቀት ስልጣኔ ጥበብ ብቻ ኣይደለም
ኣንድ ለኣንድ ሲቋቋም፥
ሰው ሰውን ገሰፀ
ሰው ሰውን በለጠ።
ደስታና ሃዘን
ኣስጨነቀው ልቡን
ከበደው መንፈሱን።
ባንድ በኩል ደግሞ ጥላቻን ኣፈራ
ምነው ያበሻ ልጅ ለምን እንዲህ ኮራ?
ምነው ምን ቸገረው
ዝንጀሮ ጦጣ ሰው
ህይወት ተመሳሳይ ምን ጊዜም ኣያጣው።
ምነው? ምን ቸገረው?[7]
ሰው ቢመስል ጦጣ፥
ቢሆንስ ዝንጀሮ፥ ኣህያና ፈረስ፥ በግ ኣሳማ ውሻ፥
ምነው ምን ቸገረው፥
ሰው ያለውን ቢለው።

---

[1]«ሰው የሚንቀሳቀስ መኪና ሆነ ሰው፥ ሆነ ዝንጀሮ» የመጀመሪያው ሃረግ የሚጀምረውም የሚጨርሰውም «ሰው» በሚለው ቃል ስለሆነ፥ ሃሳቡ «ሰው መኪና ሆነ፤ መኪናም ሰው ሆነ» ሳይሆን ኣይቀርም። እንዲያውም፥ ሁለተኛው ሃረግ ትርጉም እንዲሰጥ «ሰው» የሚለውን ቃል ከመጀመሪያው ሃረግ መበደር ይኖርበታል። ስለዚህ ኣቶ ገብረክርስቶስ «መኪና ሆነ»ን እና «ሰው»ን ሶስት የተለያዩ ሃረጎች እንዲጋርዋቸው ሆን ብለው የፃፉዋቸው ይመስላል። ሌሎች ግጥሞቻቸውን ስናነብ፥ ያልተለመዱ ያገጣጠም ዘዴዎችን ለመጠቀም ሙከራ እንዳደረጉ እናያለን። በተጨማሪም በስነ ፍጥረት (በሳይንስ) ላይ ያላቸውን ከፍተኛ እምነት እና የዘመናዊ ስእል ሊቅ መሆናቸውን ከግምት ውስጥ ካስገባናቸው ይህንን ለማመን የሚያዳግት ኣይመስለኝም።

[2]«ሲቃ ያቃጥለው ጀመር፥ ኣይኑ እያጎረጠ» ነበር የሚለው።

[3]የዚህ ስንኝ ትርጉም ኣልገባኝም።

[4]«ኣይኔ» ነበር የሚለው።

[5]«ፊታቸው» ነበር የሚለው።

[6]«ቦታቸውን» ነበር የሚለው። ኣራሚዎች «ቸ»ን ሰርዘውታል።

[7]«ምነው? ምን ቸገረው?፥ ሰው ጦጣ ነው፥ ዝንጀሮ ኣህያ ነው፥ ፈረስ በግ ኣሳማ ውሻ፥ ምነው ምን ቸገረው፥ ሰው ያለውን ቢለው።» ነበር የሚለው።

ኩራት ኣለ፥ ኩራት የህይወት፥
ትግል ብቻ፥
ኑሮ ብቻ፥
ኣይደለም ግጭት፥
ነው ጦርነት።
ሞት ነው የመረረ መብለጥ ወይ መበለጥ
መኖር ኣለመኖር[1]፥ ጉሮሮው ሲጨበጥ፥
. . . ምራቁ እያጠረ
ኣይኑ እንባ ኣቀረረ
ብስጭት ኣይደለም እልኩ ነበረ።
ነገሩን መዘነው፤
«የርጎ ዝንብ» «የርጎ ዝንብ»
ያለቦታው ሄዶ ሰው የሚጋፋበት
እትብቱ ዘመዱ ያልተቀበረበት
ባእድ መሬት፥ ባእድ . . . ።
ኣይኑ ውሃ ሆኖ፥ ቦታው ጭጋግ ለብሶ፥
ባሳብ እየዋኘ ሄደ ተመልሶ።
ኣገሩ ናፈቀው[2]
«ኣሁን ይኸን ጊዜ ኣደይ ኣበባ ነው
ደማቅ ሰማያዊ ወሩ መስከረም ነው።»
ኣጭር ነበር ጉዞው፥
የሄደው ባሳቡ፥
ወዲያው ተመለሰ
ኣይኑ እንባ ቋጠረ፥[3]
ከኣይኑ እንባ ቀረረ።

◆

# ህል - ፈተ ኣለም

ደረሰ ይሉናል ኣለም ማለፊያዋ
ዋ
የሰው ነገር ዋ
ጊዜው መቼ ገና
መች ደረሰና።
ሰው ነው በገዛ እጁ የራሱ መፍረሻ
ሌላ . . . ነገር ሲሻ
ኣይበቃኝም ብሎ ሲሰስት ሲሻማ
የሌሎቹን ኣለም ሲናጠቅ ሲቃማ
ይፈጥራል ጦርነት . . .
ይጠዛጠዛሉ ኣለማት ካለማት።
ከመሬት ጨረቃ ከጨረቃ መሬት
. . . ያቶሚኩ ርችት
ይላካል - ይመጣል
የከዋክብት መስመር ጉዞኣቸው ይናጋል።

---

[1]«መኖር ወይ ኣለመኖር» ነበር የሚለው። ኣራሚዎች «ወይ»ን ሰርዘውታል።
[2]ይህ ግጥም ብዙ የእጅ እርማቶች ኣሉበት። ኣራሚዎች የምላቸው ኣቶ ኣማረ ማሞንና ቢያንስ ኣንድ ሌላ ሰው ናቸው። እዚህ ስንኝ ኣጠገብ ሁለተኛው ኣራሚ የሚከተለውን ፅፈዋል። «ኣቶ ኣማረ እንደዚህ ቢሆንስ፡ ትዝ ኣለው መንደሩ፥ ትዝ ኣለው ገጠሩ፥ ናፈቀው ኣገሩ።»
[3]የመጨረሻው ሁለቱ ስንኞች የተኩት፡ «ኣይኑ እንባ ኣቀረረ።» የሚል ኣንድ ስንኝ ነው።

እየተፋለሰ አንዱ ኮከብ ካንዱ
አለማት ሲፈርሱ፥ አለማት ሲናዱ
ህልፈት የሚመጣው
ወዮ! ያን ጊዜ ነው።

◆

# የፆም ቀን
## የካቲት ፲፪

አገር ተቃጠለ!
እሳተ ገሞራ ወረደ ከሰለ።
ጭስ አመድ አዋራ ሰማዩን ሸፈነው
ጥቁር ሰማይ ጥቁር!
የቀን ጨለማ ሞት በእናት ቅድስት አገር
በጀግናው ህዝብ ላይ የጣላት ግፍ ቀንበር።
ፋሺስት አስተጋባ ፋስ ተሰነዘረ
ባካፋ መዶሻ ህዝቡ ተወገረ።
        የሰው ጭቅላት ኩዋስ፥ . . .
አባቶች ታረዱ፥
እናቶች ታረዱ፥
ቤት ንብረት ፈረሰ ከብቶቹ ተነዱ።
አለም መና ቀረ . . .
ውብ ለምለሙን መሬት ደም አጥለቀለቀው
ቅጠሉ ረገፈ ደረቀ ቡቃያው።
በረሃ እሳት ግለት
አሸዋ አዋራ አፈር
        ቸነፈር፥ ድርቅ[1]፥ ድርቀት
እስከ ረሃብ እጦት
ቸነፈር! ቸነፈር!
        መታሰር መጉላላት
ቅድስት ንፅህት አገር
ንፅህት እናት ሸቱ፥
                የሰው ሬሳ ክምር!
አስከሬን ባስከሬን ጥንብ የሞት ቆሻሻ
ጥንብ የሞት ጭንቀት . . .
                የጭካኔ አዝመራ
የጦርነት ፍሬ፥ ጥንብ የጣላት ሽታ!
ቅድስት ንፅህት አገር
                ኦ፥ ሰንደቅ አላማ።
ኦ፥ አንተ ነፃነት
አንተ መተባበር ኦ፥ አንተ ሆይ እምነት!
በዚች መሬት አድጎ
በዚች መሬት ሞቶ
ግፍን ተቋዋቁሞ ጠላትን መክቶ
ባላማው ለእምነቱ ራሱን ሰውቶ
ሰው ያድጋል ሰው ትልቅ
        ሰው ይሆናል ታሪክ።

---

[1]«ድርቀት» ነበር የሚለው። አራሚዎች «ድርቅ» ብለውታል።

ሌት ይነጋል መሽቶ[1]
ዘመን ሲፈራረቅ ትውልድ ይለወጣል
ይህ መሬት ቅዱስ ነው
ይህ መሬት ኣድባር ነው
የኣባቶች ውቃቢ ኣለ ያንዣብባል።
ጀግናው ልጅ ለጠላት ፊቱን ኣይመልስም
ሞት ይቀዘቅዛል ደም ሲረጋ ፈሶ
ግን ምንድነው ህይወት!
ነፃነት ለቆመ ጉልበት ተጨርሶ፤
ዘመን ያልፋል ዘመን . . .
ህሊና ይወቅሳል እምነት ሲያወላውል፥
ሃላፊነት ከባድ . . .
ያገር ንፁህ ውሃ መች ይደፈርሳል
ጠላት በወንዛችን እንዴት ይታጠባል
ድል የድል ድል ነው!
ተነሱ ዘምሩ!
እናንት የተኛችሁ መች ሞታችሁና
ይናገራል ቆሞ ስራችሁ ነውና፤
ተነሱ ዘምሩ
እዩት ልጆቻችሁ በሰማይ ሲበሩ።
እዩት የፈረሰው ተክቦ ተሰርቶ
እዩት እውቀት በርቶ
እዩት ኣገራችሁ የሺ ኣመት ጎዳና
እዩት ሄዳ ዘልቃ
እዩት ብልፅግና።
እዩት ኣገራችሁ ኮከብ ስታበራ
የባህር ኣበባ ያፍሪካ ላይ ጮራ።
ብርቅ ሉል ወርቅ ኣልማዝ፥
እና ሃገር ገነት . . .
እንግዲህ ምሽግ ነው ተራራው ኣገሬ
ወዮ ጠላት ነገ!
ወዮ ጠላት ዛሬ!
የጀግናው ልጅ ኣጥንት የተከሰከሰው
ምሽግ ነው ምሽግ ነው።
ኣጋሙ ተዋጋ ቆንጥሩ ቡዋጠጠ
የተሰነጠቀ መሬት ጠላት ዋጠ።
ዝናቡ ዘነመ፤ የደሙን ጭቅቅት –
ጎርፍ ኣጠበው ነጣ ሄደ ውሃ ይዞት።
ቡቃያው ኣሸተ
ቦምብ የገነጠለው ዛፉ ኣኮተኮተ።
ፀሃይ በራ ወጣ!
ኣንድ ኣካል ኣንድ ህዝብ . . .
ኦ፥ ሰንደቅ ኣላማ!
ኦ፥ ሃይል የነፃነት!

◆ 1950

[1]«ሲመሽ» ነበር የሚለው።

# ያለም መራራነት

ያለም መራራነት ነው የሚጣፍጠን
መች መጣፈጥዋ . . .
ኮሶውን በማርዋ ጠቅልላ ስትሰጠን
እሳቱን፥ ኣመድ ኣስመስላ ሸፍና ረመጡን፤
ስትሰጥ ማየ ህይወት፥
ስትሰጠን መድሃኒት
መርዝዋን ጨምራበት፤
ብትሰጠን ሬቱን ስኳዋር ኣስመስላ
እንደ ጎመን ሰርታ ሳማዋን ስንበላ፤
እስዋ ትዞራለች
ፀሃይ ትሞ ቃለች
እኛን በብርድ ላይ በጨለማ ጥላ።
ያለም መራራነት
የሚያቆራምድ ነው የሚያኮራምት።
ስትወስድ ወደሁዋላ፥ ስትወስድ ወደሌላ፥
ምስጢር ያላት[1] መስላ፤
ከቤተሰብ መሃል
ሰው ስታስኮበልል፤
ስትወስድ ስጦታዋን
ገፀ በረከትዋን[2]
ሌባ ናት ሰራቂ
ቀጣፊ ነጣቂ
ኣባባይ ቀልማዳ፥ ኣታላይ ኣስመሳይ
ዋሾ ናት ወላዋይ።
ሰው ሊኖር ባለም ላይ መች ተፈጠረ
መንገደኛ እንግዳ፥
መሽቶበት የመጣ፥
ሰራተኛ ኣገልጋይ፥ ነው የተቸገረ።
ብዙ ነው ልፋቱ
ሲፈጥር ሲመጣ ሲወጣ ከቤቱ።
ኣይችልም መዝናናት
በደመነፍስ ባህሪይ እንደተቀረፁት[3]
እንደ ኣህያ እንደጅብ ወይም እንደ ጦጣ፥
ወይም እንዳንበጣ፥
የማይቸገሩት ለምን ያስባሉ?
ከብቶች ይግጣሉ ወፎች ይዘፍናሉ
ኣበቦች ያድጋሉ።
ውስጡን ኣላወቁም፥ ኣልተመራመሩም
ሲመጡ ወዳለም።
የውሸት ስእል ናት፤
ለዛዋ እሚጠፋ፥
ቀለምዋ እሚጠፋ፥
ሽታዋ እሚጠፋ።

---

[1] የተፃፈው «ዳ» ይመስላል። የድሮ የፅህፈት መኪና ስለሆነ የ«ያ» እግር ከፍ ብሎ ታትሞ ነው እንጅ፥ «ያ» ነው።

[2] «ለገፀ በረከት ያበረከተችውን።» ነበር የሚለው። ኣራሚዎችም «ዜማ ይሰብራል? ወይስ ኣይሰብርም?» የሚል ጥያቄ ከጎኑ ኣስቀምጠውበታል።

[3] «እንደተፈጠሩት» ይላል የእጅ ፅሁፉ፤ ግን፥ ሰኣሊው «ፈጠረ» ከሚለው ይልቅ «ቀረፀ» የሚለውን ቃል የፈለጉበት ምክንያት ይኖራቸዋል። እነዚህ እንስሳት ከሰው ጋር «መፈጠርን» በእኩልነት እንዲጋሩ የፈለጉ ኣልመሰለኝም። «ከሰው በስተቀር ሌላው ሁሉ ስእል ነው። እግዚኣብሄርም ፈጣሪ ብቻ ኣልነበረም፤ ሰኣሊም እንጅ።» ማለታቸውም ይሆናል። እንዲያ ከሆነ ሰኣሊ በእግዚኣብሄር ኣምሳል ከተፈጠረው ሰው፥ ከፍተኛውን ደረጃ ይይዛል።

ጠረንዋ እሚያባርር፥
ጣምዋ እሚከረክር
ቡዋልትዋ የሚያስመርር።
የሰው ልጅ ኣንድ ባንድ ስታንሸራሸረው
ሁል ጊዜ እንግዳ ነው።
ማናፈስ ማቅበጥዋ
ማቻኮል ማሮጥዋ
ያለም መራራነት ነው የሚጣፍጠን
        መቸ መጣፈጥዋ!

◆ 23/9/49

# ካንቺ ጋር

ሁሉም ነገር ሄድዋል
ሰኣቱ ተረስትዋል ቀኑም ሌላ ሆንዋል
ኣመተ ምህረቱ
በጋና ፀሃዩ
        የኖርሽበት ቤቱ
ኣልጋው ጠረቤዛው ስጋጃው ወንበሩ
መስኮቱና በሩ
        ስእሉ ግድግዳው
ካንቺ ጋር ጠፍተዋል ሁሉም ተለውጠው
                                        ዛሬ ነገ የለም
ቅናትና ፍቅሩ ሃዘኑ ጨዋታው
ደስታው መከራው
                        ፈጥርዋል ሌላ ቀለም
ገርጥቶ ጠውልጎ መልኩ የነበዘ
ሞ ትዋል መታሰቢያሽ ሆንዋል የፈዘዘ።
ፈራርስዋል የካብሽው
ትዝታው የድሮው።
ቀርተሽ ተረስተሻል ጠፍተሻል ከልቤ
ወጥተሻል ከቤቴ
ወጥተሻል ካንጀቴ
ወጥተሻል ካጥንቴ
ሄደሻል ካሳቤ።
የለሽም የለሽም!
ሙዚቃ ድምፅሽን እንደድሮ ኣልሰማም።
ቅዠት ነው ዘፈንሽ ዜማሽ እንጉርጉሮሽ
ጭጋግ ነው ውበትሽ።
የጊዜው መለወጥ ገላሽን ደብቆ
                                ጋርዶታል መልክሽን
ጥላሽ ነው የቀረው ኣካልሽን[1] ተሰርቶ
                                ጨብጦ ቅርፅሽን።
ሳቅና ፈገግታሽ ጨዋታ ቀልድሽ
ለዛና ወግሽ[2]
ቅንድብሽ ሽፋልሽ የሚያበሩ ኣይኖችሽ፥
ጣፋጩ ከንፈርሽ፥

---

[1]«ኣካልሽ» ነበር የሚለው።
[2]«ወሬሽ» ነበር የሚለው። በእጅ ፅሁፍ «ወዘናሽ» ተብሎ ታርምዋል። ግን «ወዘና» ከ«ወሬ» በጣም ስለራቀ፥ «ወግሽ» ብየዋለሁ።

ለስላሳው ምላስሽ፥
በረዶ ጥርሶችሽ፥
ተለውጠው የሉም
ካሳቤ ጨለማ ገብተው ኣይታዩም[1]፡፡
ያ ውብ ቆንጆ ባትሽ
የሚቆናጠጠው የሚዋጋው ጡትሽ
የሚቆጣው ዳሌሽ!
ካንቺ ጋር ሄደዋል።

◆ 23/1/55

# መነሻ ስእል

ኣያልቅም ይህ ጉዞ . . .
        ማስመሰል-መተርጎም
በቀለም መዋኘት
በመስመር መዋኘት
ከብርሃን መጋጨት
ለማወቅ ለመፍጠር ባዶ ቦታ መግባት።
መፈለግ . . . መፈለግ . . .
ኣዲስ ነገር መፍጠር
ከማይታየው ጋር ሄዶ መነጋገር።
ህይወትን መጠየቅ
ሃሳብን መጠየቅ
ኣለምን መጠየቅ
መሄድ መሄድ መሄድ . . .
ከጨረቃ በላይ
ከኮከቦች በላይ
ከሰማዩ በላይ።
መጉዋዝ ወደሌላ - ባዶ ቦታ መግባት
በሃሳብ መደበቅ፥
መፈለግ ማስገኘት።
ኣያልቅም ይህ ጉዞ . . .

◆ 3/8/55

# ኣለ በውስጣችን

ኣለ በውስጣችን . . .
እውነት ፍፁም ሆና እምታበራበት።
ደግሞ ማወቅ ማለት፥
        ከውጪ ያለውን ሄዶ ከመፈለግ፥
ከውስጥ ያበራውን እንዲወጣ ማድረግ።[2]

---

[1]«ኣይታዩም» በእጅ ፅሁፍ የተጨመረ ነው።
[2]ከዚህ ስንኝ ቀጥሎ ባዶ መስመሮች ተትትዋል። ከዚያ ቀጥሎ የተፃፉት ስንኞች በቅርፅም በሃሳብም ከላይ ከተፃፉት ጋር ኣይመሳሰሉም። የሌላ ግጥም ቁራጭ ወይም ራሱን የቻለ ግጥም ሳይሆን ኣይቀርም።

ፍቅር፣ ተስፋ፣ ኩሩ ዝና የወጣትነት ደስታ
ተጠራርተው ብቅ ኣሉና ለጥቂት ጊዜያት ላፍታ፣
እጀብ እጀብ ኣድርገውን እንደ ቡዋልት እንደ ዋዛ
ጥፍት ኣሉ[1] እንደ ህልም፣ በነኑ እንደ ማለዳ ጤዛ።
ሆኖም ልባችን ባዶ ቤት እንዳው ብቻውን ሳይቀር
ርህራሄ ቢስ በሆነው ፈላጭ – ቆራጭ ኣገዛዝ ስር።
ያገራችንን ዋይታዋን በጥሞና ያዳምጣል፤
ፍሙ ግሎ፣ ተንደርክኮ፣ ትእግስት ኣጥቶ ይነዳል።
ፍቅር ያቃጠለው ወጣት፣ የፍቅረኛውን መምጫ ሰኣት
እንደሚጠባበቅ ተጣድፎ፣ በመቼ ደረሰችልኝ ጊዜያት!

◆ 2/5/55

# ሰው ሲሸነፍ

ማሸነፍ ምንድነው
        የምኞት ኣዝመራ
የደስታ መከራ
        የታጨደ ጣጣ
የታወቀ ችግር
        የሞተ[2] መከራ
የሚነድ እሳት ነው ተዳፍኖ የበራ
እያደር ጠፊ ነው
        እያደር ቀሪ ነው ሲቆይ ይሰለቻል
        ዋጋው ይቀንሳል[3]።
ሁልግዜ በማግኘት
ዘወትር በማሸነፍ ዘወትር በመመካት
                በመግዛት በመቅጣት፣
ደስታ ኣይገኝም፤
ሌላ ይፈልጋል የሰው ልብ ኣይጠግብም።
ለጥቅሙ የሚያስብ የተስገበገበ
መንገዱን የማያቅ ግቡ የጠበበ፣
ስስታም ይሆናል፤
ለፍቶ ጥሮ ግሮ ሲያጋጥመው እድል፣
እረፍት ኣያገኝም፤
ሲስብ ሲጠነጥን ሲታትር[4] ሲደክም።
ኣንዱን በመጨረስ ወጥኖ ሌላውን
ያንን በመሰልቸት ሲጀምር ኣዲሱን
ያቅበዘብዘዋል
        ትእግስት ይነሳዋል።
ትንሽ መሰናክል እሾህ መንገዱ ላይ
የኑሮው ህመም ነው የህይወቱ ስቃይ
ያስገባዋል[5] እልክ ደሙን ኣስቆጥቶ
ንዴቱን ኣምጥቶ።
ይተዋል ይሉኝታን ከግቡ ለመድረስ
ወዲያ ወዲህ ብሎ ሃይሉን እስኪጨርስ።

---

[1]«ኣሉ» ኣራሚዎች ያስገቡት ወሸመጥ ነው።
[2]«የሞት» ነበር የሚለው። «የሞተ» ቢሆን ካካባቢው ስንኞች ጋር ይመሳሰላል።
[3]«ይነሳል» ነበር የሚለው። ኣራሚወች «ይቀንሳል» ብለውታል። ይሻላል።
[4]«ሲታታር» ነበር የሚለው። ኣራሚዎች «ሲታትር/ሲጣጣር» ብለው ፅፈውበታል።
[5]«ያገባዋል» ነበር የሚለው።

በመሸነፍም ነው . . .
ሰው ደስታ ያለው፤
በመተው በመርሳት
በመልቀቅ በማጣት
        በመሸሽ በመፍራት።
ወደፊት ለመሄድ ኣውቆ በማፈግፈግ
ከማሰብ በብዙ ጥቂት በመፈለግ
በማነስ ከማደግ
በመጣል ከማንሳት በመስጠት ከመውሰድ
በማልቀስ ከመሳቅ
በመቅረት ከመሄድ
ከመውጣት በመውረድ
ከመልበስ መታረዝ
ከማምለጥ በመያዝ
ክብርን ለመጠበቅ ደፍሮ ከመናገር
ኣንገት በማቀርቀር፤
በመዋረድና በችግር ተጎድቶ
በመውደቅ ተገፍቶ በመናቅ ተጠልቶ[1]
በሃዘን በድካም በህመም ባርምሞ
ኣግኝቶ በመክሰር በመሻር ተሹሞ
ያውቃል መሆኑን
ይረዳል ኣቅሙን።
የህይወት ለውጥ ነው ያለበት ኑሮ ላይ
እንደ ቀን እንደ ሌት እንደ መሬት ሰማይ
እንደ ውሃ እንደ ሳት እንደ ልቅሶ ሳቅ
እንደ እርጥብ ደረቅ
ሁሉም ተለውጦ እንቅልፉን[2] ይይዛል
የሚሮጠው ጊዜ ጥቂት ይታገሳል
ሰኣቱ ይቆማል
        ደቂቃው ይተኛል
ይሸነፋል[3] ወሩ
        ይታሰራል ቀኑ
                ቀስ ይላል ዘመኑ።
የሚፈጥረው ሃሳብ ከጉዞው ሲመለስ
ያንገዋብባል መንፈስ
የምትራወጠው ትቀመጣለች ነፍስ።
ኣጥንትና ጡንቻ ጅማትና ስጋ
ዝለው ይወድቃሉ
        ሰላም ያገኛሉ
እረፍትና[4] ድካም ያሳዩታል ቤቱን
ይተኛል እንቅልፉን
ሲያውቀው መሸነፉን።

◆ 1959

[1]«ተጣልቶ» ነበር የሚለው «ተጠልቶ» ይመስለኛል።
[2]«እንደፉን» ነበር የሚለው። እንዲያ የሚል ቃል ኣላገኘሁም። የሚከተሉት ስንኞች ስለ ጊዜ ዝግ ማለት፥ መቆምና መተኛት ስለሚናገሩ፥ ቃሉ «እንቅልፉን» ሳይሆን ኣይቀርም።
[3]«ይሸፈናል» ነበር የሚለው «ይሸነፋል» ይመስለኛል።
[4]«እረፍትም ድካም» ነበር የሚለው። «እረፍትና ድካም» ወይም «እረፍትም፥ ድካምም» ይሆናል። ኣራሚዎች «እረፍትና ድካም»ን ነው የመረጡት።

# የሙዚቃ ድምፅ

የዛፉ ቅርንጫፍ የበገና ቅኝት
ነፋስ ሲያውተረትር የሚጫወትበት።
እያጨበጨቡ
ቅጠሎች በጃቸው
ዜማውን ሲያደምቁ
ወፎች ድምፃቸውን እያስረቀረቁ፥
ወንዙ እየተላጋ፥
እየተጋረፈ ሲሄድ እንዳለንጋ፥
ባህር ሲገላበጥ
እየተንጠራራ መደቡን ሲብዋጥጥ፥
መብረቅ ደመናውን ሰንጥቆ ሲወጣ
እያስገመገመ ሰማዩ ሲቆጣ፥
ሙዚቃ ተወልድዋል፤
ፍጥረት ተሰብስቦ መዝሙር ይዘምራል።
የቤቱን ቆርቆሮ
ዝናብ ሲደበድብ ኣርጎታል[1] ከበሮ።
ከሩቅ ኣገር ኣለ ደወል የሚመጣ
ከቤተ ክርስቲያን ተሰርቆ የወጣ፥
ትንንሽ ደወሎች፥
የሰኣት፥ የጥሪ፥ የተማሪ ቤቶች፥
የቀጥቃጭ መዶሻ ብረት ሲጠፈጥፍ[2]
ትልልቅ ፋብሪካ ጭሱ ሲያነፈንፍ[3]
መኪና እየጮኸ ሲሄድ ሲተላለፍ
ሁሉም ተሰብስቦ በቅደም ተከተል
ሙዚቃን ቀስቅስዋል።
ሙዚቃ ተፈጥርዋል።
ኣለ ትልቅ ጆሮ፥
ኣለ ሌላ ጆሮ፥
ይህን ሁሉ ጩኸት ሰብስቦ ኣስተባብሮ
የሚሰማው ኣለ፤
የሚወደው ኣለ።
ከቅርብ ኣውራ ዶሮ ሰኣቱን ሲያስታውስ
ድመቶች ሲጣሉ፥
        ኣራዊት ሲያስካኩ[4] ከብቱ በመላቀስ
እንጨት ሲገነጠል ሳሩ ሲርመሰመስ፥
ለሙዚቃ ስልቱ
ድምፅ ነው የሚያግዝ ተጨማሪ ምቱ።
ጥቃቅን ፍጥረቶች
ትሎች፥ ሽረሪቶች፥ ጉንዳኖች ቁጫጮች፥
ማነው ያዳመጠ ሲጮሁ ሊዘፍኑ?
ሰውም ባይሰማቸው፥
        የሚያዳምጣቸው
                ኣለ ልዩ ጆሮ፥
ኣለ ሌላ ጆሮ፥
ዜማቸውን ይዞ የሚዘምር ኣብሮ።

---

[1]«ኣድርጎታል» ነበር የሚለው።
[2]«ሲያጠፈጥፍ» ነበር የሚለው። ኣራሚዎች ደግሞ «ብረቱን ሲያጣጥፍ» የሚል ሃረግ ካጠገቡ ፅፈዋል። «ሲጠፈጥፍ» የሚሻል መሰለኝ።
[3]«ሲያነፈንፍ» ሳይሆን፥ «ፋብሪካው ጭሱን ሲነፋ» ለማለት ይመስላል። ግን፥ ቤት የሚመታ ቃል ስላጣሁ እንዳለ ትቼዋለሁ።
[4]«ሲያስካካ» ነበር የሚለው።

የሙዚቃ ድምፅ
        ኣለ ሁሉም ቦታ፥ ኣለ የትም ቦታ
ከቅጠል ኮሽታ
በውሃ ጠብታ
በንጋት በሌሊት በብርሃን በማታ
ወይ ከባዶ ቦታ።
ሲወለድ ይመጣል የሙዚቃ ስሜት፥
ከሰማይ ከመሬት፥
ይህን ሁሉ ጩኸት።
ኣለ ትልቅ ጆሮ
ኣለ ሌላ ጆሮ
ለቅሞ እያከማቸ ሰብስቦ ኣስተባብሮ፥
የሚሰማው ኣለ፤
የሚወደው ኣለ።

◆ 1959

# የጠፈር ባይተዋር

ግማሽ ቀልድ ኣላውቅም፤
        ሞት እንዲሁ[1] ልሙት፥ በሴኮንድ መቶኛ፥
እንቅልፍ እንደሬሳ ዘላለም ልተኛ።
መንገድ ስጡኝ ሰፊ . . .
ልጉዋዝ[2] ከድፍን[3] ኣጽናፍ
ልፍጠን[4] እንደብርሃን፥ ኣለማትን[5] ልለፍ፥
ፀሃይ ልሁን ፀሃይ፥
እንደ ፅርሃ ኣርያም ሁሉንም የሚያሳይ።
እሳተ ገሞራ ኣመዱ ረመጡን፥
ጎርፍ፥ የሳት ጎርፍ ልሁን፥
ከሲኦል - ሚሊዮን፥ ሚሊዮን ነበልባል።
መንገድ ስጡኝ ሰፊ . . .
ልሂድ በጨለማ ኣይን ከማያይበት[6]
ጥቁር፥ ከከሰለው[7] ከጠቆረው[8] ፅልመት
በፀጥታው ቦታ ዘመን ከቆመበት።
በዘላለማዊው ባዶ ቦታ ዋሻ፥
ኣየር በሌለበት ኣድማስ መጨረሻ።
                . . . ልንሳፈፍ ልቃኘው፥
ለኔ ኮከብ ጠጠር ኩዋስ መጫወቻ ነው።
የመሬት ቁራጭ ነኝ፤ ታሪክዋን የምፅፍ፥
                        በጥቁር ወረቀት፥ በሰማይ ብራና፥
ስጉዋዝ እየተሞላሁ በጠፈር ላይ ፋና፥

---

[1]«ሞትም እንደሁ» ተብሎ ታርሞ ነበር።
[2]«ጉዞ» ነበር የሚለው። ባካባቢው ያሉትን ስንኞች ስንመለከት «ልጉዋዝ» ይመስላል።
[3]«ከኣጽናፍ» ተብሎ ታርሞ ነበር። «ኣፅናፍ»ን «ድፍን» ያደረገው የፊደል ስህተት ነው ለማለት ያስቸግራል። የሂሳብ ሰዎች፥ «የተደፈነ/የተገደበ፥ ማለቂያ ግን የሌለው (infinite but bounded)» የሚል ኣስተሳሰብ ኣላቸው። ኣቶ ገብረክርስቶስ መጉዋዝ የተመኙት በእንደዚያ ያለ ኣለም ውስጥ ሊሆን ይችላል። ኣቶ ገብረክርስቶስ የስነ ፍጥረት ተማሪ እንደነበሩ ተነግሮኛል። ለስነ ፍጥረት ያላቸውን ፍቅርና ኣድናቆት ከብዙ ግጥሞቻቸው ውስጥ ገልፀውታል።
[4]«ፍጥነት» ነበር የሚለው።
[5]«የኣለማትን» ነበር የሚለው።
[6]«የማያይበት» ነበር የሚለው።
[7]«የከሰል» ነበር የሚለው።
[8]«በጠቆረው» ነበር የሚለው።

ስሄድ እኖራለሁ . . .
ሰማየ ሰማያት እመዘብራለሁ
የተዘጋውን በር እበረግዳለሁ።
የሌለ እስቲፈጠር፥ ዝምታ እስኪነቃ
በትልቅ እርምጃ ከመሬት[1] ጨረቃ
ከጨረቃ ኮከብ፥ ካንዱ ኣለም ወዳንዱ
ስጉዋዝ እፈጥራለሁ . . . .
በፀሃይ ላይ ጎጆ - ቤቴን እቀልሳለሁ
ከሲኦል ሚሊዮን ቢሊዮን ልቃጠል
ከገሃነም እሳት ሚሊዮን ነበልባል
መንገድ ስጡኝ[2] ሰፊ . . .

◆

# የማታ ጀምበር

ካንዱ ቤት ወዳንዱ በጣራው ተራምዳ፥
የጋራውን ኣናት እየነካች ሄዳ፥
እዩት ከስር ጥላው፥
የማይደርስበትን፥
እዩት ሰውን ጥላው፥
ሲለፋ ሲባክን።

◆

# ፊደል መጣላችሁ(ለወጣት ተማሪዎች)

የሃሳብ መግለጫ የንግግር ቁልፍ
የመተዋወቂያ የጥበብ በራፍ።
መገናኛ መንገድ ኣይነቱ የበዛ
ከሰው ልጅ መግባቢያ ትርጉም የሚነዛ
የኣለም መክፈቻ የፍጥረት ብርሃን
የሚያነጋግር ነው መስመር ቴሌፎን።
የሰማይ ምርመራ የመሬት የባህር
የመሃንዲስ ስራ ሌላም ብዙ ምስጢር
የቅኔ የዜማ ደግሞ ም የሙዚቃ
የኣቶም ምርመራ ጉዞ የጨረቃ
መገለፅ ይችላል በፊደል ምልክት
ትርጉሙን ይሰጣል ለተመራመሩት።
በቦታው ሲገባ ቃል ሆኖ ሲጣራ
«እንዲህ ነው» በማለት መንገድ የሚመራ
ለትውልድ ለታሪክ የሚተላለፍ
ፊደል ነው መሰረት የሚሆን መፅሃፍ።

---

[1]«ለመሬት» ነበር የሚለው።
[2]«ስጡን» ነበር የሚለው።

የንግግር ጥበብ ፊደል የሌላቸው
የታላቸው ፅሁፍ የቆየ ታሪክ
መድፍና መትረየስ መቼ ሰሩ ታንክ።
ኣንዱ ያቀደውን ተከትሎ ሌላው
የታለ እንደሰው፥ ልጁ የሚፈለስፈው።
የሚያስፈልገው ነው ኣንጎል ከፍተኛ
ኣስቦ ለመፍጠር ፊደል መገናኛ።
ፊደል ከጨበጠ ምላሳችሁ እጅ
ተማሪ ቤቱንም ውረሩት በይፋ
ይግባ ከቤታችሁ ፊደል በዘረፋ።
ካስተማሪ ኣንደበት ታጠቁ መረጃ
የፊደልን ስእል የፅህፈት መልመጃ።
የመሻሻል መንገድ መሆኑን ኣውቃችሁ
ተሻሙ በድፍረት ይሁን መሳሪያችሁ
ሀ ሁ ብሎ ይልቅ ንባቡ ይከተል
ቤተ መፃህፍቱ ይጥበብ ይመሳቀል
ይከፈት መፅሃፉ ይወረስ ጥበቡ
ከኣንደኛው[1] ምእራፍ ወደ ሌላው ግቡ
መፅሃፉን በመፅሃፉ ተወጡት[2] ይልቅ
በልባችሁ ወፍጮ ተይዞ ይድቀቅ።
ይበዝበዝ ይራቆት ይቅር ይዘረፍ
ባንጎላችሁ ጋሻ በኣእምሮኣችሁ ሰይፍ
በፊደል መሰላል፥ በንባብ ጎዳና
ኣሳዱት የሚያመልጥ የለም ፍልስፍና።
ከገባበት ጉድጉዋድ ኣውጡት ጎትታችሁ
«የተማሪ ሰነፍ» እንዳያሰኛችሁ።
ተሳተፉ እንግዲህ ተማሩ ኣሁን
ቀለም ያመጣውን መምህር ንባቡን[3]።
ይኸውና ፊደል መሳሪያ መያዣው
የጥበቡ ሳጥን ቁልፉና መክፈቻው።

◆

# እጠብቃታለሁ

ኣይን የማያየውን ሃሳብ ያያል ሄዶ
እጅ የማይነካውን ልብ ያንቃል ኣሳዶ።
ተመለሽ ኣልልም
ሞት ለያይቶን እንደሁ
ያባት ያያት ርስት
የመጨረሻው ቤት፤
ለፀጥታው ኣለም
እንግዳ ኣይደለንም፤
መለየት እንደሆን፥
ለይቶ ያስቀረን
ሃሳብ ይላላካል፥
ሃሳብ ይገናኛል፤

---

[1]«ካንደኛው» ነበር የሚለው።
[2]«ውጡት» ነበር። በእጅ ፅሁፍ ታርምዋል።
[3]«ንብ ኣቡን» ነበር የሚለው።

ኣይን የማያየውን ሃሳብ ያያል ሄዶ
ጆሮ የማይሰማውን
በፀጥታ ቦታ
ልብ ያንቃል ኣሳዶ።[1]
ማን ያውቃል ለሞትም
ይኖራል መቃብር
ጉዞ ኣያቁዋርጥም።
ኣለም እያረጀ ኣለም ይፈጠራል
ኣበባ በፍሬው ህይወትን ያድሳል
የፅጌረዳ እሾህ ያበባው ጠባቂ
ሳቂ የለም ሳቂ፥
እሾህ እሆናለሁ
የምወዳትን ልጅ እጠብቃታለሁ
በቁም ያሰረኝን የሃሳብ ሰንሰለት፥
ሰብሬ በጥሼ እኮበልላለሁ
እስካለም ዳርቻ እከተላታለሁ።
ሳላያት ኣልቀርም፥
ኣለ ስጦታዋ፥
ኣለ ትዝታዋ እስዋን የሚያስታውስ፥
ስበላ፥ ስጠጣ
ስተኛ ስነቃ፥ ሳስብ፥ ስተነፍስ፤
እስዋን መርሳት ኣልችል
ፍቅር እምነት ህይወት፥
ኣብረን ተደስተን ኣብረን ተቸግረን
ኣበባ ለቅመናል ከወንዝ ዳር ሄደን።
እሸት ፈልፍለናል
መስክ ላይ በልተናል፥
ልብሳችን በሰብሰቦ በዝናብ ርሰናል[2]።
እሳት ኣንድደናል፥
ፍሙን ተርኩሰናል፤
በርድዋት ተኮራምታ ህፃንዋ ጨረቃ፥
ፊትዋ ደም ሲመስል ፀሃይ ተዘቅዝቃ፤
ሁሉንም ኣይተናል፥
በሁሉም ስቀናል፥
ህይወት እንደዚህ ነው
ኣለም ነው ብለናል።
እርስዋን መርሳት ኣልችል
እፈልጋታለሁ፥
እከተላታለሁ
እጠብቃታለሁ።

◆

[1]ይህንን ስንኝ፥ ከሁለተኛው ስንኝ ቀድቼ እዚህ የጨመርኩት እኔው ነኝ። ተተይቦ ያገኘሁት ግጥም ውስጥ ኣልነበረም። ግን «ኣይን የማያየውን ሃሳብ ያያል ሄዶ» የሚለውን ስንኝ ስለደገሙት፥ ቤት መምቻውንም ስንኝ ኣብረው የሚደግሙት ይመስለኛል። ምናልባት ገልባጮች እረስተውት ይሆናል።
[2]«ሄደናል» የሚለው በእጅ ፅሁፍ «ርሰናል» ተብሎ ታርምዋል። ይሻላል።

# እኔ እወድሻለሁ

ብዙ ሺህ ዘመናት
እልፍ ኣእላፍ ሌሊት
ሚሊዮን መሰለኝ
ፍቅሬ ኣንችን ስወድሽ ቀኑ ረዘመብኝ።
እኔ እወድሻለሁ
የሰማይ መሬቱን
የባህር ስፋቱን
የኣለም ዳርቻ የርቀቱን ያህል
እንደ ፅጌ–ረዳ
እንደ ኣደይ ኣበባ
እንሎሚ ሽታ።
እንደእጣን ጢስ እንጨት፥ እንደከርቤ ብርጉድ፥[1]
እኔ[2] እወድሻለሁ፥
ኣበባ እንዳየ ንብ።
እንደቢራቢሮ ጫካ እንደሚያስሰው
ፍቅርሽን በፍቅሬ በፍቅርሽ ልቅመሰው
ማር ወለላዬ ነሽ ከረሜላ ስኩዋር
ኣማርኛ ኣይበቃ፤
ወይጉድ!
ባለም ቁዋንቁዋ ሁሉ ቢወራ ቢነገር፥
እኔ እወድሻለሁ
እንደማታ ጀንበር።
እንደ ጨረቃ ጌጥ፥
እንደንጋት[3] ኮከብ፥
እኔ እማልጠግብሽ
ስወድሽ፥ ስወድሽ፥ ስወድሽ፥ ስወድሽ።
ጡት እንዳየ ህፃን ወተት እንዳማረው
ጠጋ በይ ዘመዴ ኣፍሽ ህይወቴ ነው።
ጣይ እንዳየ[4] ቅቤ
ገላዬ ገላሽን ሲነካ የሚያልቀው፥
ኣፈር መሬት ትቢያ ወሃ እንደሚበላው፤
ፍቅሬ ኣንቺን ስወድሽ
ብዙ ሺህ ዘመናት
እልፍ ኣእላፍ ሌሊት
እኔ እወድሻለሁ፤
ኣይኖችሽን ባይኔ ተዳክሜ እያየሁ
ስወድሽ ስወድሽ
እኔ[2] እወድሻለሁ።

◆ 16/9/1960 የኢትዮጵያ ድምፅ ጋዜጣ።

---

[1]«እንደከርቤ ብርጉድ፥ እንደእጣን ጢስ እንጨት» ነበር የሚለው። ኣልገጥም ስላለኝ፥ ሃረጎቹን ኣዘዋውሬኣቸዋለሁ።
[2]«ውድ» ነበር የሚለው።
[3]«እንደተወርዋሪ ኮከብ» ነበር የሚለው። «እንደንጋት» ተብሎ ታርምዋል።
[4]«ጣይ ላይ ያለ ቅቤ» ነበር የሚለው።

# የፍቅር ፍልስፍና

ጅረቶች ከወንዞች ጋር፥ የሙጥኝ ብለው . . .
ተጣምረው
ወንዞችም ውቅያኖስ ኣቅፈው
የሰማየ ሰማያት ንፋስ፥ ጣፋጭ ስሜት ሲዋሃደው . . .
ተመልከችው።
ከቶ ኣንድም ነገር በኣለም ላይ፥ ያላቻ ያለጓደኛ . . .
ሆኖ ኣይገኝም ብቸኛ።
በውስጠ ምስጢር ህላዌው፥ ይጣመራል ሁሉም በውል፥
በኣንድ መንፈስ፥ በኣንድ ቃና፥ ስጋና ደሙን ሲያዋውል።
እኔና ኣንቺስ ምናለበት፥
ኣንድ ብንሆን ብናውቅበት።
እንደ መሶብ ከግጣሙ፥
ተራሮች ሰማይ ሲስሙ . . .
እይው ጣእሙ።
ማእበሎችን እያቸው፥ ባህር ላይ ሲሽከረመሙ፥
ሲላላሱ ሲተሻሹ፥ ኣንዱ ባንዱ ውስጥ ሲሟሙ፤
ኣንዱ ማእበል ኣንደኛውን፥
ኣቅፎት ሲሄድ ኣቻውን . . .
እይው በሞቴ ጣእሙን።
ደግሞም የፍቅር ጡር ጣጣ፥
ሴቴ ኣበባ ያለወንዱ፥ ኣበባነቷ ቅጥ ሲያጣ፥
ወንዴ ኣበባም ያለሴቷ በፀሃይ ሃሩር ሲቀጣ፥
እይው ቆንጆት፥ እይውማ፥
ልቦና ፍቅር ሲጠማ።
የፀሃይ ብርሃን ጠዋት፥ የመሬትን ከንፈር ሲስም፥
በሙቀት እየዳበሰ፥ ፈገግታዋን ሲያለመልም . . .
ለዛው ሲፈካ ሲተም።
የጨረቃ ጨረር ሞገድ፥ የባህርን ራቁት ገላ፥
በምሽት የእንቅልፍ ሰኣት፥ ይደበዝዛል እያጠላ።
ስለዚህም ኣስተውይው፥ እኔን ሁኝ ኣንችን ልሁን፥
በደም ስርሽ ደሜ ይፍሰስ፥ በደም ስሬ ደምሽ ይሁን . . .
ኣንድ እንሁን!!

◆

# የመጀመሪያ ቀን

ኣየቺው ተያዩ
ኣየና ወደዳት
ቀኑ ማታ ነበር
ወደ ሆቴል ሄዱ
ሁለት እራት መጣ
ብርጭቆው ተጋጨ
ኣየቺው ተያዩ
ኣያት ተሳሳቁ

በጠረጴዛ ስር
ጭንዋ[1] ጭኑን ነካው
ኣየችው ፈገገ
እጅዋን[1] በእጁ ያዘው
ጠበቅ ኣደረጋት
ጠበቅ ኣረገችው[2]
ከፈሉና ወጡ
በከሰለው[3] ሌሊት
ሁለቱ ነደዱ
ታፋቸውም[4] ጋለ
ቤቱ ተቃጠለ
ፍራሹ ነደደ
ፍቅር ተያያዘ

◆

# ያገረሸ ፍቅር

የሰማይ ኣሞራ፥
ላዋይህ ችግሬን፥
ብረር ሂድ ንገራት፥
ከትልቁ ዛፍ ስር፥
ድሮ በልጅነት፥
ከተጫወትንበት[5]፥
ከትልቁ ዛፍ ስር ኣታጣትም ፍቅሬን፥
ብረር ሂድ ንገራት፥ ንገር መናፈቄን።

◆

# የፍቅር ቃጠሎ

ጉንጭሽ ፅጌረዳ፥
ሞቆት የፈነዳ፥
ኣይንሽ የጥዋት ጨረር
የበራ ማለዳ።
የማትጠገቢ የስንዴ ራስ ዛላ፥
ኣገዳ ጥንቅሽ፥
ጠብ ኣትይ ኣንጀቴ፥ ባኝክ ብመጥሽ።

---

[1]ይህ ግጥም ሁለት ቦታ ተፅፎ ኣግኝቼዋለሁ። የተተየበው (በፅህፈት መኪና የተፃፈው) ኗ፥ ጇ ሲል፥ የታተመው (የጋዜጣ ቅጂ ይመስላል) ግን ንዋ፥ ጅዋ ይላል። ጋዜጣው የታተመው ኣቶ ገብረ ክርስቶስ እያሉ ከሆነ፥ የዚህ ኣይነቱን የኣፃፃፍ ዘዴ እንደማይቃወሙ መገመት ይቻላል።

[2]ግጥሙ «ኣደረገችው» ነበር የሚለው። ለማንበብ ስለሚያስቸግር ለውጬዋለሁ።

[3]ጥቁርነትንና ጨለማን ብዙ ቦታ ከከሰል ጋር ያመሳስሉታልና፥ ምናልባት ስእል የሚሰሩበት "*charcoal*" የሚሉት የጥቁር ከሰል እርሳስ እየታያቸው ይሆናል፥ የሚል ግምት ነበረኝ። ዶክተር ፍቅሬ ቶለሳ ግን፥ እዚህ ግጥም ውስጥ ያለው «ከሰል» የሚያመለክተው የሌሊቱን ጥቁርነት ሳይሆን ግለቱን ነው፥ ብለውኛል። ይመስላል።

[4]«ታፋቸው» የሚለውን፥ ለማንበብ ስለሚያስቸግር ታፋቸውም ብየዋለሁ።

[5]«ከተጨዋወትንበት» ነበር የሚለው።

ቆንጆ ነሽ ኣንቺዬ
        እሳት ነበልባል ነሽ፥ ንዳድ በኣከላቴ
ሆነሻል ሙቀቴ፥
        ሆነሻል ህይወቴ።
የጋለው ትንፋሽሽ፥
የሞቀው ምላስሽ፥
ማርኮኝ በከንፈርሽ፥
እጄን ሰጥቻለሁ፥
እስረኛ ሆኛለሁ።
ያንቀጠቀጠኛል ወባ ቅናት ገብቶ፥
ልቤን ኣስፈራርቶ
ትኩሳት ኣምጥቶ።
ፍቅርሽ ኣቃጠለኝ፥ በመልክሽ ልተክዝ፥
እቀፊኝ ልቀዝቅዝ፥
                ንከሽኝ ልደንዝዝ።

◆ 11/3/51 የዛ.ኢ.

# ዛሬ ወዴት ኣለ?

ቅኝ ኣገር መሻማት ዛሬ ወዴት ኣለ?
የመርከብ ወንበዶች ጊዜኣቸው የታለ?
እንደዱሮ ኣይሆንም
ታሪኩ ቢወራ ሃተታው ቢለቀም
እንደጥንቱ ኣይሆንም።
መሰሉም ቢመጣ ጥቂት ተለውጦ
                        «ታሪክ ተደገመ!»
ይባላል ሲጠፋ ጊዜ እየታመመ።
በራሱ ከረጢት ገብቶ ተጠቅልሎ
ለብቻው ሲደበቅ ሸሽቶ ተገልሎ
ኣስታዋሽ ሲያገኘው
እየታየ ጥላው
ሁሉም ይለወጣል ጊዜ እየቆጠረ
ኣንዳንዴም ይረሳል እየተሰወረ።
ጨረቃ እንደክብሪት ፀሃይ እንደሻማ
                        በርተው ይጠፋሉ
ተቃጥለው ያልቃሉ።
ሰማይ ተቀዳዶ እንዳሮጌ ሸማ
        ከዋክብት ኣንድ ባንድ ወድቀው ተንጠባጥበው
የባህርይ ፍጥረቶች እንዳልነበር ሆነው
ሲመጣ ጊዜያቸው
ያልፋሉ ጨልመው።
የማይቀር ምን ኣለ?
የማይቀር ምን ኣለ?
ሞትም ሙት ይሆናል የሚሞት ሲጠፋ
ጊዜም እየገፋ
የሚገፋው ሲያጣ ይሆናል የጠፋ።

◆ ገብረ ክርስቶስ ደስታ።

# ምስጢር

ሁሉም እንደዘበት
ሁሉም በዘልማድ
ሁሉም እንዲያው፥ እንዲያው
የሚሆን መስሎሃል፥
ጉንዳንን ተመልከት -
የወፍ ቤትን ኣጥና -
ንቦችን ኣስተውል -
ኣንድ የውሻ ጩኸት ሙዚቃ እየሆነ. . .
ኣለምን በመዞር ሌሊቱን ያነጋል።

◆

# ትንኝ

በቅንድቤ ክብደት
ትንኝዋን ፈጨሁዋት
ጎርፍ እንባ ወረደኝ . . .
ኣይኔ መቼ ወዶ
የተለመደ ነው ሃዘንና ፀፀት
ኣውቀው ባደረጉት
ሳያውቁ በሰሩት።
ምን ቀን ቀጠሮ ነው
ኣይኔን ከመጠጠኝ[1] . . .
ከዚህ ሁሉ ቦታ
ከዚህ ሁሉ መሬት
ከዚህ ሁሉ ሰማይ
ኣይኔ ተገልጦ እንዲያይ
ትንኝ እንዲገባ . . .
ሞት እጁን ዘርግቶ ህይወት እንዲቁዋረጥ
ሰበብ እኔ ልሆን
በማላውቀው ነገር
ባልፈለግሁት ነገር
ምን ጠባብ ኣለም ነው
ኣክ እንትፍ ኤጭ ወዲያ
ምን ጨካኝ ኣለም ነው።

◆

[1]«ከመጠጠኝ» ይሆን? መኮምጠጥ ደግሞ ለምላስ እንጅ ለኣይን ኣይሆንም። የተለምዶ ስርኣትን የሚያፋልሱ ሃሳቦች ሌሎችም ግጥሞቻቸው ውስጥ ስለሚገኙ፥ ቃሉ «ከመጠጠኝ» ቢሆን ኣይገርመኝም። በዘመናዊ ስእል ውስጥ ይህ ኣሰራር የተለመደ ነው። ለምሳሌ ኣንድን ደረጃ ኣቅጣጫውን ሳይለውጥ ወደታች የሚወርድ እንዲሁም ወደላይ የሚወጣ ኣስመስለው ይስሉታል።

# ፍቅር ጥላ ሲጥል[1]

በገና ቢቀኙ
ሸክላ ቢያዘፍኑ
ክራር ቢጫወቱ . . .
ለሚወዱት ምነው
ሙዚቃ ቢያዜሙ
ቃል ቢደረድሩ
ጌጥ ውበት ቢፈጥሩ
ቤት ንብረት ቢሰሩ
ኣበባ ቢልኩ
ምነው ቢናፍቁ
ኣገር ቢያቋዋርጡ
ቢሄዱ ቢርቁ
ኣመት ቢጠብቁ . . .
ለሚወዱት ምነው?

◆ ጥር 1 ቀን 1955 ኣ.ም

# ሃገሬ

ኣገሬ ውበት ነው፥
ለምለምና ነፋስ የሚጫወትበት፥
ፀሃይ የሞላበት፥ ቀለም የሞላበት።
ኣገሬ ቆላ ነው፥ ደጋ ወይና ደጋ፥
እዚያ ብርሃን ኣለ ሌሊቱ እስኪነጋ።
ኣገሬ ተራራ ሸለቆ ረባዳ፥
ኣገሬ ጅረት ነው ገደልና ሜዳ፥
ውበት ነው በበጋ ፀሃይ ኣትፋጅም፥
ክረምቱም ኣይበርድም፥
ኣይበርድም፥ ኣይበርድም።
ኣገሬ ጫካ ነው፥
እንሰሳት ኣራዊት የሚፈነጩበት፥
በወጥመድ ሳይገቡ ሳይነካቸው ጠላት።
እዚያ ኣለ ነፃነት፤
በሃገር መመካት፥
በተወዳጅነት፥
በባለቤትነት፥
እዚያ ኣለ ነፃነት።
ኣገሬ ሃብት ነው፤
ኀመኑ ስብ ጮማ፥ ቆሎው ክትፎ ስጋ፥
ድርቆሹ ፍትፍት ነው፤ ቃርያው ሙክት ስጋ።
ጠጁ ነው ወለላ፥
ከኮኛክ ያስንቃል የመንደሩ ጠላ።
እህሉ ጣእም ኣለው፥ እንጀራው ያጠግባል፥
ከቢራ ከሻምፓኝ ውሃው ይጣፍጣል፥

---

[1]ከመጨረሻው «ለሚወዱት ምነው?» ከሚለው ስንኝ በስተቀር፥ እያንዳንዱ ቃል ኣንድ ኣንድ መስመር ላይ ነበር የተፃፈው። ምክንያቱ ስላልገባኝ ከላይ በተቀመጠው መልኩ ኣንብቤዋለሁ።

በኣሉ ይደምቃል፥
ሙዚቃው ያረካል፥
ጭፈራው ዘፈኑ ችግርን ያስረሳል።
እዚያ ዘመድ ኣለ፤
ሁሉም የናት ልጅ ነው፥
ሁሉም ያባት ልጅ ነው፥
ጠላትም ኣንዳንዴ ይመጣል መቃብር፥
ባለጋራም ቸር ነው «ያገር ልጅ» ሲቸገር፤
ገነት ነው ኣገሬ።
ምነው ምን ሲደረግ?
ምነው ለምን እንዴት?
ዘራፊ ቀማኛ ምቀኛ ወንበዴ፥
ጥርኝ ኣፈር በጁ ስንዝር ወሰን ኣልፎ፥
የተቀደሰውን ያፍሪቃ ላይ ደሴት፥
ባያገኝ ለማርከስ ጠላት ይመኝ እንዴት።
እምቢኝ ኣሻፈረኝ፥
ኣሻፈረኝ እምቢ፥
መቅደስ ነው ኣገሬ፥
ኣድባር ነው ኣገሬ፥
እናትና ኣባቴ ድኸው ያደጉበት፥
ካያት ከቅድም ኣያት የተረካከቡት፥
ኣፈር የፈጩበት፥
ጥርስ የነቀሉበት።
ኣገሬ ኣርማ ነው፥ የነፃነት ዋንጫ፥
በቀይ የተጌጠ ባረንጓዴ ቢጫ።
እሾክ ነው ኣገሬ፥
በጀግናው ልጅ ኣጥንት የተከሰከሰ፥
ጠላት ያሳፈረ ኣጥቂን የመለሰ።
ኣገሬ ታቦት ነው፥ መቅደስ የሃይማኖት፥
ዘመን የፈተነው በጠበል በፀሎት።
ለምለም ነው ኣገሬ፥
ውበት ነው ኣገሬ፥
ብሞት እሄዳለሁ ከመሬት ብገባ፥
እዚያ ነው ኣፈሩ፥ የማማ ያባባ።
ስሳብ እሄዳለሁ ቢሰበርም እግሬ፥
ኣለብኝ ቀጠሮ፥ ከትውልድ ኣገሬ።
ኣለብኝ ቀጠሮ፥
ከትውልድ ኣገሬ፥
ካሳደገኝ ጓሮ።

◆

# እንደገና

ይናፍቀኝ ነበር . . .
ዞሮ ዞሮ ከቤት
ይላል የኛ ተረት።
ኣብዋራው ፀሃዩ ይናፍቀኝ ነበር
ኣፈሩ ጠጠሩ ይናፍቀኝ ነበር

የመንደር ጭስ ማታ . . .
ይናፍቀኝ ነበር የሳር ቤት ጥቀርሻው
መደቡ ምሰሶው
ማገሩ ግድግዳው፥ ኣጥሩና ጥሻው።
የፈራረሰ ካብ . . .
ቀጭን ጠባብ መንገድ በመንደር የሚሮጥ
ቅጠል የሸፈነው
ሳር የለበሰው፤
እነዚህ እነዚህ ይናፍቁኝ ነበር
የተቆላ ቡና
የሚወቀጥ ቡና
የጎረቤት ቡና፥ ኣቦል ሁለተኛ
የተረጨ ቆሎ የሚያርቅ መጋኛ
የሚጨሰው እጣን . . .
እንጀራ በመሶብ ወጥ የፈሰሰበት
ያገልግል እንጀራ የሚብዋጠጥ ፍትፍት
የክክ ወጥ የሽሮ
የስጋ የዶሮ
ይናፍቀኝ ነበር ቅራሪ ጉሽ ጠላ
ይናፍቀኝ ነበር ፊልተር ዞሚኮላ
ያገራችን ድግስ . . .
ከበሮ ጭፈራው
ዝላዩ እስክስታው ስካሩ ሁካታው
ትርኪ ምርኪ ነገር ግፊያው ትንቅንቁ
ኩዋኩዋታው እርግጫው ዘፈን ድብልቅልቁ
«ኣሸወይና ወይና» . . .
«እሲቲ እንደ ጎጃሞች»
«ኣሲዮ ቤሌማ» . . . «ኣሆሆ፥ ኣሃሃ»
የቄስ ትምርት ቤት[1]
የህፃናቱ ድምፅ
ሀ ሁ ሂ ሃ ዜማ ነበር የናፈቀኝ
የፅጌ ጭፈራ ነበር የናፈቀኝ፤
ከበሮ ፀናፅል
ሆሳእና ጥምቀት
ፋሲካና ገና ሁዳዴና ስግደት
ቡሄ ሆያ ሆዬ
የእስላሞች ኣረፋ፥ የጋላ ሸጎዬ
የቁልቢው ገብርኤል
ልደታ
ፍልሰታ
ኣውቆ የበቀለ ወፍ ዘራሽ ኣበባ
ለምለም ኣረንጉዋዴ . . .
ያልተጠበቀ መስክ ከብት የሚግጥበት
የደመና ግላጭ የሚጫወትበት፤
ሌላም ብዙ ነበር
ሌላም . . . ደግሞ ሌላ
ያገር ሰው ነበር እኔን የናፈቀኝ
የቀይ ዳማ ነበር፥ ጥቁር ቆዳ ነበር
ቁርንጫጭ ከርዳዳ፥ ዞማ ጠጉር ነበር
ያገራችን ቁዋንቁዋ . . .
ያገሬ ሙዚቃ ያገራችን ዜማ
ጥበብ እጀ ጠባብ ያገራችን ሸማ

[1]«ት/ቤት» ነበር የሚለው።

ነበረ ናፍቆቴ ለሁሉም ለሁሉ
        ለሸዋ ለወሎ ለትግሬ ቤገምድር
ለጎጃም ወለጋ ላሩሲ ኢልባቦር
ኤርትራ ገሙጎፋ
ለሲዳሞ ከፋ
ለሁሉም ለሁሉም ነበረ ናፍቆቴ፥
                        ኣለብኝ ትዝታ።
ዘመዶቼ ሳሙኝ
ጉዋደኞቼም ጋብዙኝ
ሊስትሮ ጨብጠኝ
ባለጋሪ ንዳ መንገዱን ኣሳየኝ
ያገሬ ልጅ ቆንጆ «ቤት ለእንግዳ» በይኝ።
ኣለብኝ ትዝታ . . .
        ኣዲስ ኣበባ ላይ ነበረ ናፍቆቴ
                መናገሻ ነበር እንጦጦ ነበረ
ኤረር ጋራ ነበር ዝቁዋላ ነበረ
ገፈርሳ ነበረ ጉለሌም ነበረ
ኣዲሱ ከተማ . . .
        «መርካቶ ዲጂኖ ችምችም ያለው መንደር»
የከተማው እንብርት ደጃች ውቤ ሰፈር።
የቸርቸር ጎዳና
የባቡሩ ጣቢያ
ቢሾፍቱ ነበረ ናዝሬት ሞጆ ኣዋሽ
ድሬዳዋ ነበር
ኣለማያ ነበር
ሃረርጌ ነበረ የተወለድኩበት
እናትና ኣባቴን ጥዬ የሄድኩበት
የሚካኤል ጉዋሮ
        ሃረርጌ ነበረ
                ዞሮ ዞሮ ከቤት . . .
ሃገሬ ነበረ እኔን የናፈቀኝ
ኢትዮጵያ ነበረች።

◆

# ለቡጊ

በግሬ ጣራ መርገጥ
ሙዚቃ ሲጋልብ መውጣት መውረድ መፍረጥ
ኣይኔን ማገላበጥ
መርበትበት መንቀጥቀጥ
መላጋት መንገድገድ እንደሰከረ ሰው
የናፈቀኝ ይህ ነው።
ተነስቼ ልዝለል
ቡጊ ቡጊ ልበል . . .
ቡጊ ቡጊ ቡጊ
        ከበሮ ሲያጋፍት ሙዚቃ ሲያናፋ
ልብሴን ጥዬ ልጥፋ።
ልራቆት ኣብጄ
ልብረር ካለም ሄጄ።

ሙዚቃ በጥላው ይምጣ ይሸፍነኝ
ሁሉንም ያስረሳኝ።
እንደሳት ቦግ ቦግ[1]
መውለብለብ መንተግተግ፣
መቃጠል መሞት ነው
ይህ ነው፣ ዳንሴ ይህ ነው።
ልቤን ይነሳኛል . . .
ዛር ይሰፍርብኛል
ልወርውር እጆቼን
　　　　ሙዚቃን እንደኩዋስ ልለጋው በግሮቼ
ልዝለል ተነስቼ፤
ቡጊ ቡጊ ልበል
መሬት ልንከባለል፣
ልዝለል ጮቤ ልምታ
ያቃዠኝ ኣንዳፍታ፤
ቡጊ ቡጊ ቡጊ

◆

# እረፍት ኣድርግ ኣሁን (ለኣባቴ)

እንቅልፍህን ተኛ
　　　　　　　　የዘላለም እንቅልፍ . . .
እንዳይቀሰቅስ . . . ህ
የዚህ ኣለም ፀሃይ የሚያጭበረብረው
ኣይንህን ኣይንካው፤
የዚህ ኣለም ስቃይ፣
　　　　የዚህ ኣለም እንቅልፍ የሚያባንነውን
እርሳው የኔ ኣባባ . . .
　　　　ውሸቱን ኣትስማ ከበሮ ፀናፅል፣
　　　　　　　　　　　　　　　　ፍታቱን ልቅሶውን፤
ደረት መጥጠፍጠፉን[2] ፀጉር መነጨቱን
ኣፈሩ ሲከብድ የድንጋዩ ጭነት
　　　　　　　　　　　　ግባ–ተ መሬቱን፤
እርሳው ኣባብዬ . . .
　　　　ኣታስብ ይበቃል።
ድሮም ኣንተ እንደዚህ ብዙ ጊዜ ኣይተሃል
ኣንተም ኣባት ሞቶህ፣
　　　　ኣንተም እናት ሞቶህ
　　　　　　　　ኣንተም እህት ጠፍቶህ
　　　　　　　　　　　　ሚስት የልጆች እናት . . .
　　　　　　　　　　　　　　　　እንባህን ጠርገሃል።
ታውቃለህ ብዙ ነው፣ መንገዱ ብዙ ነው።
ሞት እንደንቆቅልሽ
　　　　ጅምሩ ማለቂያው
　　　　　　　　መካከሉ ዳር ነው።

---

[1]«ቦግ ቦግ» የሚለውን፣ ኣራሚዎች «ቡግ ቡግ» ኣድርገውት ነበር።
[2]«ሲጠፈጠፍ» የሚለውን ኣራሚዎች ለውጠውታል።

ታውቃለህ ሰው ኢምንት
ሰው ጥቃቅን ነገር
ሲኖር የማይታይ
በሚሊዮን እጥፍ
በሚሊዮን ጊዜ በጣም ካላጎሉት
/ታውቃለህ የኔ ኣባት ኣስተምረኸኛል/
በመኖር በመሞት
ልዩነት የሌለው
ቢኖርም ልዩነት
ከነፋስ ከውሃ መልኩ የቀጠነ
ኣይን የማይጨብጠው
ህይወትን ሲያነቡት ወደ ግራ ሞት ነው፤
/ብለህ ነግረኸኛል፤/
ስለዚህ ግድ የለም
እንቅልፍህን ተኛ።
በፀጥታ ቦታ ካሳብ ኣልፎ ተርፎ
ሃሳብ ይኖር ይሆን?
ግድ የለም . . . መመርመር ኣትሞክር።
ኣንተ[1] ሁን ፀጥታ
ህይወት የዘራውን የጤና[2] ቡቃያ
በበሽታ ኣመዳይ ሞት እንደሚያጠፋው
በወዲያኛው ኣለም የፀጥታን ክዳን
ቢኖር ልዩ ነገር የሚቀሰቅሰው
ኣትንቃ ከእንቅልፍህ፥
በመብረቅ ነጎድጉዋድ ኣለም[3] ይደባለቅ
ሰማይ መጋረጃው ይተርተር ይሰንጠቅ
ፀሃየ ፀሃያት ኮከብ ይንጠባጠብ፤
ጨለማም ይጨልም ኣይኑ ኣውቆ እስኪጠፋ
መሬት ጭቃ ኣዛባ ሊጥ ትበጥብጥ
ሌዋታን[4] ይንቀጥቀጥ
ብሄሞት[5] ይንቀጥቀጥ
ሳጥናኤል ይቆጣ ሲኦል ኣፉን ይክፈት
እልፍ ኣለም ይቃጠል በገሃነም እሳት[6]
መንግስተ ሰማያት ባልማዝ ሉል ታብረቅርቅ
ገነት ትፍካ ትሳቅ
ጉዳይህ እንዳይሆን።
ድሮ በልጅነት . . . በጎልማሳነቴ . . .
ኣደንቅህ ነበረ[7]።
ያ ድምፅ የእውቀት ደወል
የሃይማኖት ዜማ የህይወት ሙዚቃ
ሃያል ግርማ ሞገስ፤
ያ በሰው ልጅ ኣምሳል የተጎናፀፍከው
ያ መመራመርህ . . .
ኣስተዋይነትህ
ኣደንቅህ ነበረ።
ድሮ በንግግር፥ ድሮ በትምህርት
ጥበብ እውቀት ሆነህ ፀሃይ ብርሃን ሆነህ

---

[1]«ኣንተ» ብሎ ያለው ቃል በደንብ ኣይታይም።
[2]«የጠና» ነበር የሚለው፤ ሊሆንም ይችላል። ግን ሞት የሚያጠፋው በበሽታ ኣመዳይ ስለሆነ፥ ጠፊው ጤንነት ሳይሆን ኣይቀርም።
[3]«የለም» ነበር የሚለው። «ዓለም»ን እንጽፋለን ብለው ይመስለኛል ተያቢዎች «የለም» ያሉት።
[4]ሌዋታን=ግዙፍ የባህር ውስጥ ኣውሬ ወይም ትልቅ ውቅያኖስን የሚያቁዋርጥ መርከብ።
[5]ብሄሞት=ጉማሬ ወይም እንደሰው ማሰብና መናገር የማይችል እንስሳ።
[6]«ሳት» ነበር የሚለው።
[7]«ነበር» የሚለው በእጅ ፅሁፍ ታርምዋል።

ኣሁን ጊዜው ሲመሽ . . .
የድሜ ሳት ተቃጥሎ ከሰል ሲሆን ህይወት
ኣሁን በዝምታህ
ኣሁንም ኣያለሁ፤
ኣያለሁ በፊትህ
ኣይኔ በንባ ርሶ
የውበት ፈገግታህ ኣልጠፋም ጨርሶ፥
ትዝታህ ኣልጠፋም፤
ደግነትህ ኣለ።
እውነ ክርስቲያን እውነ ሳምራዊ
ቅዱስ ትህትና ቅዱስ ሰማያዊ
ድካምክን ኣውቃለሁ።
ድካምህ ልፋትህ
ላገር ለወገንህ፥
ለህግ ለነፃነት
ለምነትህ ለእውነትህ
ሳቅ፥ ኣሁንም በሞት
/እዚህ የሌለ ሳቅ/
በፀጥታው ቦታ ሙዚቃ ሁንበት
/ዝም ያለ ሙዚቃ/
እረፍት ኣድርግ ኣሁን።

◆

# ሰው ነው የረቀቀ[1]

ሰው ነው የረቀቀ
ከሜርኩሪ ቬነስ፥ ከጨረቃ ከማርስ
ከፕሉቶ ኔፕቱን፥ ኡራኑስ የላቀ
ከጁፒተር ሳተርን፥ ከጣይ[2] የደመቀ
ባካባቢው ሁሉ እያሸበረቀ፥
ሰው ኣደገ ኣወቀ፥
መሬት እንቁላሉን ሰበረ መጠቀ፤
ሰው ኣለምን ኣየ . . .

በጨለማው ቦታ ዶቃ ኣንፀባራቂ
ውብ ሰማያዊ ኩዋስ፥ ሮዝ[3] ኣብረቅራቂ።
በተጣራው ኣየር በነጣው ደመና
ባረንጉዋዴው ባህር ውሃ ተሸፍና[4]፥
ውብ ሉል ኮከብ ኣለም፥ የጠፈር ላይ ጤዛ፥
የሰው ልጆች እናት፥ የሰው ልጆች ቤዛ።

◆ መስከረም 1961 ኣ.ም

---

[1] ይህ ግጥም ሁለት ቦታ ተፅፍዋል። መጀመሪያ «የጠፈር ባይተዋር» ከሚለው ግጥም ጋር ከሌላ ቦታ ደግሞ ለብቻው «ሰው ነው የረቀቀ» በሚል ርእስ ስር። ከጠፈር ባይተዋር ጋር ስናነፃፅረው ኣይስማማም። ራሱን የቻለ ግጥም ይመስላል።
[2] «ፀሃይ» ነበር የሚለው፤ ሊሆንም ይችላል። «ሰው ራሱ የደመቀ ፀሃይ ነው።» ለማለት ከሆነ። ግን የኣካባቢውን ስንኞች ስንመለከት፥ «ሰው፥ ከፀሃይ ይበልጥ የደመቀ ፍጡር ነው።» ለማለት ይመስላል።
[3] «ውብ ሮዛዝ» ነበር የሚለው።
[4] «ባረንጉዋዴው ኣጣቢ ውሃ ተሸፍኖ» ነበር የሚለው።

# ኣንተ ነህ መስከረም

ማለቂያ በሌለው ደማቅ ሰማያዊ
ከሩቅ ያለው ጋራ ተነክሮ ሃምራዊ
በዚያ ላይ ደመናው እንደጥጥ ተነድፎ
እየተራራቀ ቢያንዣብብ ተቀጥፎ
ኣንተነህ መስከረም
የሃምሌን ጨለማ የነሃሴን ዝናም
የሻርከው ኣንተነህ
በብርሃን ፈገግታህ
በክረምቱ ወራት ሰማዩን ያስጌጠው
የማርያም መቀነት በቀለም ያበደው
ጤዛው ነካክቶታል መሬቱ ላይ ለቆ
በቀይና ቢጫ መስኩ ተለቅልቆ
ወንዙና ጅረቱ ድንጋይና ኣፈሩ
ኣገሩ ውብ ሆንዋል ሜዳው ሸንተረሩ
እንቁጣጣሽ ኣንተ ስሞታህ የበዛ
ለሰው መታሰቢያ ውበት የምትገዛ
በሽቱ መኣዛህ ለውጠው ኣመቱን
ይታደስ ያረጀው ፍጥረት ሌላ ይሁን
ከምረው ዘመኑን ካበው ባመት ባመት
በወሩ ደረጃ ፍጥረት ይጉዋዝበት
ፍየሎች ይዝለሉ ቅጠል ይበጥሱ
ከተሰደዱበት ወፎች ይመለሱ
ይልቀሙት እህሉን
ይስሩ ቤታቸውን
ይስፈሩበት ዛፉን
የደስ ደስ ያሰሙ ንቦች ይራኮቱ
ይንጠራሩ ኣበቦች ይንቁ ይከፈቱ
እምቦሳና ግልገል በሜዳው ይፈንጩ
ከብቶች ሳሩን ይንጩ
ህፃናት ይሩጡ ይሳቁ ይንጫጩ
ዛፎች ይተንፍሱ
የነፋሱ ጠረን . . .
ይሰራጭ በቦታው ያውደው ኣገሩን።
ኣደይ ኣበባ ነህ የመስቀል ዳመራ
ጠረንህ ኣልባብ ነው ኣየርህ የጠራ
ያገር ልብስ ኣንተነህ ነጭ እንደበረዶ
ሰው የሚያጌጥብህ ጥበብህን ወስዶ
ቡቃያ ነህ እሸት ጉዋሚ[1] የበሰለ
ኣረንጉዋዴ ለብሰህ በጌጥ የተሳለ
ጥቁር ኣረንጉዋዴ
ቢጫማ ኣረንጉዋዴ
ያተር ኣረንጉዋዴ
ቅጠል ኣረንጉዋዴ . . . ቀለም ቀለም ቀለም
የሚስተካከልህ የሚያስንቅህ የለም።

---

[1]«ጉዋሚ» የሚል ቃል ኣላገኘሁም። መዝገበ ቃላቱ ውስጥ ሁለት ተቀራራቢ ቃሎች ኣሉ። ኣንደኛው፥ «ጉዋሚያ (=ያልበሰለ ፍሬ)» ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ «ጐሚት (=የሚያምር ኣበባ)» ናቸው። ያካባቢው ስንኞች የሚገልጹት ያማሩና የደመቁ ቀለሞችን ስለሆነ ቃሉ «ጐሚት» ይሆናል ብየ ኣስቤ ነበር። ግን «ጉዋሚያ» የተሻለ ምርጫ ነው። «ቡቃያ ነህ እሸት» የሚለው ሃረግ ያንድን ሂደት መጀመሪያና መጨረሻ ወይም የሁለት ቅራኔዎችን ኣንድ ላይ የመገኘት ጠባይ ነው የሚያሳየው፤ «ልጅም ነህ ኣዋቂ» እንደማለት። ስለዚህ ሁለተኛው ሃረግ «ጉዋሚያ የበሰለ» ቢል ያስኬዳል፤ «ጥሬም ነህ ብስል» ማለት ይሆናልና።

ሃዘን የምታርቅ የገነት ምሳሌ
ይታደል ወለላህ ጠጅ በብርሌ
ይስከር በደስታ ህዝቡ ይሳሳቅ
ድምፁ እየተመታ ሙዚቃው ይፍለቅ
እንቁጣጣሽ ብለን እንስጥህ ሰላምታ
የዘመኑ መሪ የወሮቹ ጌታ
ይጨብጨብ ለዝናህ
ይጨብጨብ ለስራህ
ይጨብጨብ ለመልክህ
ኣንተ ነህ መስከረም
ዘመን የምታድስ ኣስጊጠህ በቀለም።

◆

# ቀረሽ እንደዋዛ

እንደ ድመቶቹ
የትም እንደሚያድሩት
እንደ ስልክ እንጨቶች
እንደዛፍ ሃረጎች
እንደቤት ክዳኖች
ብርድ ኣቆራመደኝ
ስጠብቅ ጥጠብቅ
«ትመጫለሽ ብዬ ሳይ ማዶ ሳይ ማዶ
የልጅነት ኣይኔ ሙዋሙዋ እንደበረዶ»
ትመጫለሽ ብዬ ደቂቃ ስቆጥር
ትመጫለሽ ብዬ ሰኣቱን ስቆጥር
ትመጫለሽ ብዬ ባዝን ባንጎራጉር
ትወጫለሽ[1] ብዬ በበራፍሽ ብዞር
ብርድ ኣቆራመደኝ
የመንገድ መብራቶች ኣይተው ኣፌዙብኝ
ውርጩ ቀለደብኝ
ጨለማው ሳቀብኝ።
ኣለመምጣትሽን
ኣውቀዋል ያውቃሉ
መስኮቶች ጨልመው
ቤቶች ተቆልፈው
ከተማው ሲተኛ
ኣይተዋል ያያሉ
ኣለመምጣትሽን
ኣውቀዋል ያውቃሉ።

◆

---

[1]«ትመጫለሽ» ነበር የሚለው። የፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ለውጥ ነው።

# ኢዮሃ!

ኢዮሃ!
አበባ ፈነዳ!
ፀሃይ ወጣ ጮራ
ዝናም ዘንቦ አባራ
ዛፍ አብቦ አፈራ፤
ክረምት መጣ ሄደ
ዘመን ተወለደ
አዲስ አለም ሆነ።
ሌሊት ሲነጋጋ . . .
ጋራው ድንጋይ ከሰል
የተንተረከከ ፍም እሳት ደመናው፥
ፀሃይ ያነደደው።
አለም ሞቆ
ደምቆ፥
ብርሃን ሲያሸበርቅ
ጤዛው ሲብረቀረቅ፥
ህይወት ሲያንሰራራ
ፍጥረት ሲንጠራራ፥
ዘመን ተለወጠ መስከረም አበራ።
«ኢዮሃ አበባዬ።»

◆ 1955